# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 257 ግንቦት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# “የመንግሥት ዋና አላማ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን መደገፍና ማብቃት ነው”

- አቶ አህመድ ሽዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

**ጌትነት ተስፋማርያም**



ፎቶ-ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት ዋና አላማ ከውጭዎቹ ኢንቨስትሮች ይልቅ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን መደገፍና ማብቃት ላይ ያተረኮረ ነው ሲሉ የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሽዴ ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት “ስለኢትዮጵያ” በሚል ስያሜ ያሰናዳውና በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮረው የድሬዳዋ የፓናል ውይይት ሰሞኑን ሲካሄድ አቶ አህመድ ሽዴ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌሎች አገራት ኢንቨስትሮች በተሻለ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጽኑ ፍላጎት አለው።

የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ለኢኮኖሚው ያስፈልጋሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሁለቱንም በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ፓርኮችም ውጤት ማምጣት ተችሏል። ይሁንና የመንግሥት ዋና አላማ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን በመደገፍና በማብቃት አቅሙ እንዲጠናከር ማድረግ ነው ብለዋል።

መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ በሚያደርግበት ወቅት ብዙውን ጊዜ በውጭ ባለሀብቶች ወቀሳ ሳይቀር ሲቀርብበት ይስተዋላል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይሁንና ከሀገር በላይ ምንም የለምና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ዘርፉ በበላይነት በእነሱ እንዲመራ ለማድረግ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀሙ ጠቃሚ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ድጋፍ ይደረግለታል ሲባል ግን ኢንዱስትሪው በሀገር ውስጥ አቅም ብቻ ይሳካል ብሎ ማሰብ አይገባም ሲሉ ተናግረዋል።

ምክንያቱም የፋይናንስ፤ የቴክኖሎጂና መሰል አቅማችን ገና ውስን በመሆኑ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅቶ መስራት ያስፈልገናል። በመሆኑም ሁለቱም ተቀናጅተው እንዲሰሩ መደገፋችንን እንቀጥላለን ብለዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪውም ሆነ የአገልግሎት ዘርፉ የሚያድገው በዋናነት በግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በመንግሥት በኩልም መሠረተ ልማትን ማስፋት፣ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ አቅም በፈቀደው ልክ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቁመዋል።

የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ቢሮክራሲ በማቅለል ረገድ የተሻለ ስራ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ አቅም ሲጠናከር መዋዕለ


“የመንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል













# ከማዕድን ዘርፉ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት በትኩረት እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

## - ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ማዕድናት 458 ሚሊየን ዶላር በላይ ተገኝቷል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከማዕድን ዘርፉ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘትና ዘርፉን በብርቱ የሚፈታተነውን የፀጥታ ችግር ለመፍታት ከፀጥታ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር ገለጸ።

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በትናንትናው ዕለት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 9ኛ መደበኛ ስብሰባ የዘጠኝ ወር ሪፖርት አቅርበዋል።

በበጀት ዓመቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ማዕድናት 458 ነጥብ 07 ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል። በተመሳሳይ ወቅት ሲሚንቶ ፋብሪካዎች 8 ነጥብ 2 ሚሊዮን ቶን ለማምረት አቅደው


ከማዕድን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ-ኢዮብ ተፈራ

ኢንጂነር ታከለ ኡማ

# ‹‹የሕግ የበላይነት ማስፈን የህልውና ጉዳይ በመሆኑ አጥፊዎች ለህግ እንዲቀርቡ ይደረጋል››

- ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ
በሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የህግ የበላይነትን ማስፈን ለድርድር የማይቀርብ የመንግሥት ጽኑ አቋም በመሆኑ አገር ለማፍረስ እየሰሩ ያሉ አጥፊዎች በህግ እንዲጠየቁ እንደሚደረግ በሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ዶክተር ቢቂላ ሁሪሣ ገለጹ።

ዶክተር ቢቂላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የህግ የበላይነትን ማስፈን ለድርድር የማይቀርብ የመንግሥት ጽኑ አቋም በመሆኑ አገር ለማፍረስ እየሰሩ ያሉ አጥፊዎች በሕግ እንዲጠየቁ ይደረጋል።

የሀገሪቱን ሰላም ለማናጋት ብሎም አገር በኃይል ለማፍረስ ሲሰሩ የነበሩና እየሰሩ ያሉ ሕወሓት አመራሮች ሳይቀሩ ሁሉም አጥፊዎች ለህግ የሚቀርቡበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆንም ጠቁመዋል።

ጽንፈኝነትና አክራሪነት የትኛውንም ብሔር የማይወክል አደገኛ አዝማሚያ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ አስተሳሰቡም ሆነ ድርጊቱ የአገር ሁለንተናዊ እንቅቃሴን የሚገታና መዘዙም ህዝብ ላይ የሚከፋ መሆኑን አስገንዝበዋል። በአገሪቱ የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ መንግሥት የህልውና ጉዳይ አድርጎ እንደሚሰራም አመልክተዋል።



የአንዳንድ ኃይሎች አገር የማፍረስ ዓላማ ወደፊትም አይሳካም ያሉት ዶክተር ቢቂላ፤ መንግሥት የአገር ህልውና ለመታደግና መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገውን የህግ የማስከበር እንዲሳካ ህዝቡ


“የሕግ የበላይነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







አቶ ናሆም ስንታየሁ

# ማዕከሉ በወቅታዊ ቁመናው ወረፋ የሚጠብቁ ታማሚዎችን ለማስተናገድ 13 ዓመታት በላይ ይፈጅበታል

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- አሁን ባለው አቅሙ ከቀጠለ ተመዝግበው እየተጠባበቁ ያሉትን ሰባት ሺህ ሁለት መቶ በላይ ታማሚዎች ለማስተናገድ ከአስራ ሶስት አመት በላይ እንደሚፈጅበት የልብ ህሙማን መርጃ ማዕከል አስታወቀ።

የማዕከሉ የህዝብ ግንኙነት ተጠሪ አቶ ናሆም ስንታየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ተመዝግበው እየተጠባበቁ ያሉትን ታማሚዎች ለማስተናገድ አሁን ባለው አቅም ሲሰላ በትንሹ አስራ ሶስት አመታት ያስፈልጉታል።

ማዕከሉ ለመታከም ወረፋ የሚጠብቁ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ በላይ ታማሚዎች ቢኖሩትም የልብ ህሙማን መርጃ ማዕከል ዓመታዊ የማስተናገድ አቅሙ በአንድ አመት ውስጥ 550 ታማሚዎች ብቻ መሆኑን የገለጹት አቶ ናሆም፤ ማዕከሉ በስሩ የሚታከሙ የልብ ህሙማን በሙሉ የማስተናገድ አቅም እንደሌለውም ገልጸዋል።

አቶ ናሆም የልብ ህሙማን መርጃ ማዕከል ህሙማኑን ለመደገፍና ለመርዳት ያለውን አቅም ሁሉ አሟጦ በመጠቀም ላይ እንደሚገኝ በመጠቆም፤ በአማካኝ በሳምንት ለዘጠኝ ህፃናት የህክምና አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝም አመላክተዋል።

በማዕከሉ የመታከም እድል የደረሳቸው ታማሚዎች አብዛኛዎቹ የመዳን እድል ያላቸው ሲሆን፤ ህፃናቱ ቀላል ቀዶ ጥገና በመደረግ ሊድን በሚችል ህመም ወደ ማዕከሉ ሄደው ወረፋ በመጠባበቅ በመቆየታቸው ምክንያት ለቀዶ ጥገና የሚከብድበት ደረጃ ላይ ህመማቸው ሊደርስ እንደሚችልም ገልፀዋል።

ማዕከሉ በሚገባው መጠን ታማሚዎችን ለማስተናገድ በመጣር ላይ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ናሆም፤ የሚያስተናግዳቸውን ህሙማን መጠን በአመት አንድ ሺህ አምስት መቶ ለማድረስ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ላይ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

ለልብ ህክምና ወረፋ የሚይዙ ህፃናት የመታከሚያ ተራቸው ሳይደርስ የመሞት እድል እንዳላቸው የገለፁት አቶ ናሆም፤ ማዕከሉን ለማጠናከር ባለድርሻ አካላት በዘርፉ ተሳትፎ ሊያደርጉ እንደሚገባና የግል ህክምና ተቋማት ዘርፉን በመቀላቀል የማዕከሉን ውጥረት በማቃለል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸውም ነው የገለጹት።

በኢቲዮ ቴሌኮም አማካኝነት በነፃ ለህሙማን መርጃ ማዕከሉ በተከፈተው የፅሁፍ መልእክት መላኪያ 6710 አማካኝነት ህዝቡ የሚያሳየውን ርብርብ እንዲቀጥል የተናገሩት አቶ ናሆም፤ ማህበረሰቡ በ6710 ላይ አንድ ብር በመላክ ህሙማኑን እንዲረዳም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

# ከ50 በመቶ በላይ እሴት የተጨመረባቸው ተሽከርካሪዎች ለውጭ ገበያ ቀረቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ከ50 በመቶ በላይ እሴት የተጨመረባቸው እና በአዲሱ የንግድ ምልክት ወደ ገበያ የገቡ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች ፍራንኮን በተባለው ድርጅት ለውጭ ገበያ ተላኩ።

ፍራንኮን የተባለው ድርጅት ለ15ኛ ዙር ከባድ መኪናዎችን ለውጭ ገበያ ማቅረቡን በተመለከተ በወዳጅነት አደባባይ ባዘጋጀው ማሳያ ላይ የተገኙት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፤ አምራቾች በስራቸው ጊዜ የሚያጋጥማቸውን መሰናክል ተቋቁመው በማለፍ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ፋይዳቸውን በማይናጋ መሰረት ላይ ለመጣል መስራት አለባቸው ብለዋል።

አምራች ኢንዱስትሪዎች ለሚገጥሟቸው ችግሮች እጅ መስጠት ሳይሆን ለችግሮቹ የመፍትሔ ሀሳብ አፍላቂዎች መሆንና ያጋጠሙ ችግሮች ለስራ መሻሻልና ዕድገት ጠቃሚ ግብዓቶች አድርጎ በመውሰድ ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ አመላክተዋል። ፍራንኮን የጀመረው ስራ ተስፋ ሰጪ መሆኑንም ተናግረዋል።

የድርጅቱ መስራችና ስራ አስኪያጅ አቶ ፍራንችስኮ ቪሎኒ ድርጅቱ ከተቋቋመ 10 ዓመታትን ያሳለፈ መሆኑን ገልጸው፤ እስከ አሁን ከ15 በላይ የሚሆኑ መኪናዎችን ወደ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሱዳን እንዲሁም ወደ ኡጋንዳ ሀገራት ለውጭ ገበያ መላካቸውን አብራርተዋል።

ፍራንኩን 60 በመቶ የሀገር ውስጥ ምርት በመጠቀም የመኪናዎች የአካል ክፍል እንደሚያመርት የተናገሩት አቶ ፍራንችስኮ፤ ለሀገር ውስጥ ገበያ ከ200 በላይ ተሽከርካሪዎችን ሰርተው መሸጣቸውን እና በቀጣይም 67 የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎችን ለመሥራት ትዕዛዝ መቀበላቸውን አስረድተዋል።

ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ በሚገባበት ወቅትም ለ320 ዜጎች የስራ ዕድል ይፈጥራል መባሉን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል።




# በድር ኢትዮጵያ 22ኛ ኮንፈረንሱን በመጪው ሐምሌ ወር በአዲስ አበባ እንደሚያካሂድ አስታወቀ

## . ለታላቁ ህዳሴ ግድብ በጎ ፈንድ ሚ በተከፈተ አካውንት አንድ ሚሊዮን 50 ሺ ዶላር ድጋፍ አድርጓል

ሞገስ ተስፋ

በአዲስ አበባ፡- በድር ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሙስሊሞች ማህበር 22ኛ ኮንፈረንሱን በመጪው ሀምሌ ወር "በድር ወደ ማንነት"(Badr back to the root) በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ እንደሚያካሂድ አስታወቀ። በድር ኢትዮጵያ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ በጎ ፈንድ ሚ በተከፈተ አካውንት አንድ ሚሊዮን 50 ሺ ዶላር ድጋፍ አድርጓል።

ኮንፈረንሱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሰከነ መንገድ በመወያየት ችግሮችን ነቅሎ ለማውጣት ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሔ ማምጣት እንደሚቻል ለማሳየት ያለመ ነው።

የበድር ኮንፈርንስን አስመልክቶ በአዲስ አበባ የተቋቋመው ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ በሽር መሐመድ እንደገለጹት፣ በድር በዓለም ላይ የተቋቋሙ ከ20 በላይ ድርጅቶችን ያቀፈ ሲሆን 22ኛውን ኮንፈረንሱን ከሀምሌ 8 እስከ 18 ድረስ በአዲስ አበባ ለማካሄድ ዝግጅት ተደርጓል።

እንደ አቶ በሽር ገለጻ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ የሚካሄደው ኮንፈረንስ ዋና አላማ ከኢትዮጵያ ውጪ የተወለዱ ሁለተኛ ትውልዶችን ወደ አገራቸው በማምጣት ስለአገራቸው በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው የማስተዋወቅ፣ ኢትዮጵያውያን ስለ አገራቸው ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሰፉና የተለያዩ ስራዎችን እንዲሰሩ ነው።

22ኛው ኮንፈረንሱን ከሀምሌ 8 እስከ 18 ድረስ "በድር ወደ ማንነት"(Badr back to the root) በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ የገለጹት የንዑስ ኮሚቴው ሰብሳቢ፤አባላትና ቤተሰቦቻቸው በኢትዮጵያ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ በመሰማራት ለአገር ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው።

በድር ኢትዮጵያ ከአባይ ንጉሶች ከኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ጋር በመተባበር በጎ ፈንድ ሚ በተከፈተ አካውንት ለታላቁ የህዳሴ ግድ አንድ ሚሊዮን 50 ሺ ዶላር ድጋፍ ማደረጉን አቶ በሽር ተናግረዋል።

የዝግጅት ኮሚቴው አስተባባሪ አቶ መሐመድ ካሳ በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ የበድር ኮንፈረንስ ኢትዮጵያን የማያውቁ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን በመጎብኘት ስለአገራቸው ታሪክ እንዲያውቁ ማስቻል ነው። ኮንፈረንሱ በኢስላማዊ ስነስርዓት ላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሰከነ መንገድ በመወያየት ችግሮችን ነቅሎ ለማውጣት ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሔ ለማምጣት አላማ ያደረገ ነው።

በተጨማሪም በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ከመንግሥት የተለያዩ ተቋማት ጋር ውይይት የሚደረግ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ የበድር ቢሮ በመክፈት ዘርፈ ብዙ የበጎ አድራጎት ስራ ላይ ለመሰማራት ይሰራል ብለዋል።

የኮንፈረንሱ መካሄድ በኮቪድና በጦርነቱ ምክንያት የተቀዛቀዘውን የኮንፈረንስ ቱሪዝምን የሚያነቃቃ ሲሆን፤ ጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄዱ ኢትዮጵያውያን የተቀዛቀዘውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማነቃቃት የሚረዳ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት ጉዞ "እስላማዊ እሴቶች ለኢትዮጵያ ባህልና እድገት" በሚል ወደ አገራቸው እንደሚመጡ የገለጹት አስተባባሪው፤ በኮንፈረንሱ የተለያዩ ጥናታዊ ጹሁፎች ይቀርባሉ። ከአምስት ሺ በላይ አባላትን ያቀፈው በድር ለኮንፈረንሱ ከአንድ ሺ 500 በላይ ሙስሊሞች የተመዘገቡ ሲሆን አባላቱ ከነቤተሰቦቻቸው በመምጣት ይሳተፋሉ ብለዋል።

# የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት በፍትሐዊነት በማከፋፈል አምራቹን መደገፍ እንደሚገባ ሚድሮክ አስታወቀ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት በፍትሐዊነት በማከፋፈል አምራች ኢንዱስትሪዎችን ይበልጥ መደገፍ እንደሚገባ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "ስለኢትዮጵያ" በሚል ስያሜ በድሬዳዋ ከተማ ያሰናዳውና በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮረው የፓናል ውይይት ሰሞኑን ተካሂዷል። በወቅቱ የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃላፊ አቶ ጀማል አህመድ እንደገለጹት፤ አምራች የግል ባለሀብቶችን ይበልጥ ለመደገፍ በግሉ ዘርፍ የሚቀርበውን የውጭ ምንዛሬ በፍትሐዊነት ማከፋፈል ይገባል።

በተለያዩ ጊዜያት እንደሚታየው በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ዕጥረት አለ በሚባልበት ወቅት በዚያው ልክ ደግሞ የቅንጦት ዕቃዎች በብዛት ወደአገር ውስጥ ይገባሉ። ፋብሪካዎች በመለዋወጫና በግብዓት ዕጥረት በሚዘጉበት አገር የቅንጦት ዕቃዎች በብዛት መግባታቸው የውጭ ምንዛሬ ድልድል በፍትሐዊነት እንደማይቀርብ ያሳያል ብለዋል።



አቶ ጀማል አህመድ

ደሃ ሀገር ላይ እንደመሆናችን የጥሬ ዕቃ ችግር አለብን፤ በመሆኑም ከፍተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልገናል ያሉት አቶ ጀማል፤ ይህን አይነት ችግር ያለበትን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መንግሥት ለመደገፍ የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም በውጭ ምንዛሬ ጉዳይ ላይ ያለውን ችግር ማስተካከል ግን ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

ችግሮች በአንዴ አይፈቱም ቢሆንም ግን ለውጭ አገር ባለሀብቶች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ለአገር ውስጥም ሊሰጥ ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል መንግሥት የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲበረታቱ ለዓመታት ያከናወነው ስራ በተለያዩ ዘርፎች የግል ባለሀብቱ እንዲጠናከር አቅም መፍጠሩን ገልጸዋል።

በዚህም የተነሳ በሌሎች የአፍሪካ አገራት ላይ ከአገሬው ሰው ውጪ የሚያዙ ዘርፎች አሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እራሳችንን ወክለን ምርታችንን እንገበያያለን ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይ በሌሎች የአፍሪካ አገራት በማይታይ መልኩ በቡናና በተለያዩ ምርቶች ላይ የሀገራችንን ቡና ይዘን ለገበያ እንቀርባለን። ሌላው አፍሪካ ሀገር የሀገራቸውን ቡና ይዞ የሚቀርበው የውጭ ዜጋ ነው። የኢትዮጵያን ቡና እኛው ይዘን በዓለም ገበያ ስንቀርብም ኩራት ይሰማናል፤ ይህ እንዲሆን የመንግሥት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም ብለዋል።

ሚድሮክ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ላኪዎች ሁሉ ከፍተኛ ምንዛሬ የሚያመጣ ኩባንያ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በመሆኑም በህጋዊነት የሚሰሩ ኩባንያዎችን ይበልጥ በፋንይናስ አቅርቦት በመደገፍ ምርታማነትን ማሳደግ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ አቶ ጀማል ገለጻ፤ መንግስት የማኑፋክቸሪንጉን ዘርፍ አቅም ለማሳደግ እያከናወነ ያለው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች በጎ አካሄድን እያሳዩ ይገኛል። ሚድሮክም ለዚህ የምርታማነት ማሳደግ ስራ ከሌሎች ተቋማትና ከመንግስት ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ ነው።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ መንግሥት የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን ቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ያመነጩትን የውጭ ምንዛሬ መጠቀም እንደሚችሉ በህግ መፈቀዱን ገልጸዋል።

መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የለውጥ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ግን የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

# ቡና ወደ ቻይና በመላክ 30 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር ተገኘ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም በአስር ወር አፈጻጸም ከ5 ሺህ ቶን በላይ ቡናን ወደ ቻይና በመላክ 30 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር አቶ ታጠቅ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የምትሰጣቸው እድሎች በርካታ መሆናቸውና ከቻይና ጋር ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት የቡና ገበያው በቻይና ገበያ እንዲያድግ አድርጎታል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቡና በቻይና ገበያ ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በ2014 ዓ.ም ወደ ቻይና 5 ሺህ 8 መቶ 79 ቶን ቡናን በመላክ 30 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።። በ2013 ዓ.ም 5 ሺህ 1 መቶ 48 ቶን ቡናን በመላክ ከተገኘው 23 ነጥብ 16 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ጋር ሲነጻጸር በመጠንና በገቢ የ3 በመቶ እድገት ማሳየቱን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ቡና በቻይና ገበያ ሊያድግ የቻለው ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላት ግንኙነት ጠንካራና መልካም መሆኑ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በሀገራት መካከል ግንኙነት እያደገ በመጣ ቁጥር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩ እየጠነከረ ይሄዳል ብለዋል። ኤምባሲዎች በበይነ መረብ የሚያደርጓቸው ኤግዚቢሽኖች፣ አምባሳደሮች የሚያደርጉት እንቅስቃሴና እንደሀገር የተዘረጋው የንግድ ፖሊሲ የቡና ገበያውን እንዳሳደገው ገልጸዋል። እንዲሁም ለገዥዎች ስለ ኢትዮጵያና ስለቡናዋ የሚሰሩት የማስተዋወቅ ስራዎች ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ገልጸዋል።

በተለይ የኢትዮጵያ ቡና እንደ ቅመም ለሌሎች ቡናዎች ማጣፈጫነት ስለሚጠቀሙባቸው በበርካታ ሀገራት የመፈለግ ባሕሪያቸው እየጨመረ መምጣቱን አስረድተዋል። በቻይና በሌሎች ሀገራት የኢትዮጵያን ቡና የመግዛት ፍላጎታቸው እያደገ በመሆኑ ኢትዮጵያም ከአረቢካ ቡና አምራች ሀገሮች ጋር ተወዳድራ በተሻለ ጥራት ማቅረብ ከቻለች ገበያውን የመቆጣጠር እድልን እንደሚፈጥርላት አስረድተዋል።



እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ባለ ልዩ ጣዕም ቡናዎች በቻይና፣ በኮርያ፣ በጃፓንና በታይዋን እየተፈለጉ መምጣታቸው ወደፊት ከፍተኛ መዳረሻዎች ይሆናሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸዋል። በተለይ ወጣቱ ትውልድ ቡናን የመጠቀም ልምዱ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመሆኑና የኢትዮጵያን ቡና እየተቀበሉ ያሉ ሀገራት ሀብታም ሀገሮች በመሆናቸው ለቡና ከፍተኛ ብር ያወጣሉ። ልዩ ጣዕም ያላቸው ቡናዎች የኑሮ ደረጃ መለያም እየሆኑ በመምጣታቸው ለኢትዮጵያ ቡና ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን ገልጸዋል።

ቡና ላኪዎቻችን የአሜሪካ ተጠቃሚዎች ነበሩ ማለት አያስደፍርም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አሜሪካ በብዛት ለኢንዱስትሪ ምርቶች ነው እድል ይሰጥ የነበረው። ለግብርና ምርት እድል ቢኖርም ግንዛቤ ኖሮ ከመጠቀም አንጻር አነስተኛ ነበር። ነገር ግን አሜሪካ በብዛት ጥራቱን የጠበቀ ቡና የምትጠቀም በመሆኑ የኢትዮጵያ ቡና በአሜሪካ ገበያ ይሸጣል እንጂ በቀጥታ ከአጎዋ ጋር አይገናኝም።

በ2014 ዓ.ም ወደ አሜሪካ 18 ሺህ 8 መቶ 51 ቶን ቡና በመላክ 110 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።። በ2013 ዓ.ም 14 ሺህ 9 መቶ 76 ቶን ቡና በመላክ 77 ነጥብ 15 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን አስታውሰው፤ ካለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 8 በመቶና በገቢ 11 በመቶ እድገት ማሳየቱን ጠቁመዋል።

# በከተማዋ የሚስተዋሉ ሕገወጥ ማስታወቂያዎች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ ከ155 ሺ በላይ ህገ ወጥ ማስታወቂያዎች ላይ እርምጃ መወሰዱንና በቀጣይም እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን አስታወቀ።

የባለስልጣኑ የቅድመ መከላከልና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ የአብነህ ገዳሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ የሚስተዋሉ ህገወጥ ማስታወቂያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ ነው። በመሆኑም ባለስልጣኑ እነዚህን ህገወጥ ማስታወቂያዎች ለመከላከል በትኩረት እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ህገወጥ ማስታወቂያዎች አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንደሚያሳጡ ገልጸው፤ በህብረተሰቡ ውስጥ ነውር የሆኑ ተግባራትን በማበረታታትና ሰዎችን በማይጨበጥ ደመወዝ በማጓጓት ለህገወጥ ሥራና ለጉልበት ብዝበዛ እንዲዳረጉ በማድረግ በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ነው። ይህንን ህገወጥነት ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ ነው ብለዋል።

ባለስልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ የማስታወቂያ ድርጅቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ዳግም የመመዝገብ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

ባለስልጣኑ ህገወጥ ድርጊቶች ከተፈጸሙ በኋላ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ አስቀድሞ መከላከል ላይ አተኩሮ ይሠራል። ይህም እንደ አገር ሊደርስ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ለመቀነስ እንደሚያግዝ አመልክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን ማስታወቂያ ስታንዳርድ እያዘጋጀ መሆኑን የጠቆሙት አቶ የአብነህ፤ በስታንዳርዱ ምን አይነት ማስታወቂያ? የቱ ጋር? በምን መልክ? መቀመጥ አለበት ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል። ይህን ለማስፈጸም ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው



አቶ የአብነህ ገዳሙ

ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ህገወጥ ማስታወቂያዎች የሚለጠፉበት ሁኔታ የከተማዋን ውበት በእጅጉ የሚያደበዝዝ ነው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ አንዳንድ ቦታ ላይ የእግረኛ መንገዶች ተቆፍረው የሚተከሉበት ሁኔታ እንደሚስተዋል ተናግረዋል።። ስለዚህ ይህ ነገር በስታንዳርድ መመራቱ የከተማዋን ውበት ከመጠበቅ ባለፈ መሠረተ ልማቶችን ከጉዳት ለመጠበቅም ያስችላል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ህብረተሰቡን ካልተገባ መረጃ ለመጠበቅ ጉልህ ሚና እንዳለው አመልክተው፤ አገሪቱ ከዘርፉ ተገቢውን ገቢ እንድትሰበስብ እንደሚያግዝም ተናግረዋል።

ባለስልጣኑ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተቋሙን በሰለጠኑና በብቁ ባለሙያዎች ለማደራጀት በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

ህገወጥ ተግባራትን በመከላከል በኩል የህብረተሰቡ ሚና ትልቅ መሆኑን አስታውሰው፤ ዜጎች በየአካባቢያቸው ሲፈጸሙ የሚያስተውሏቸውን ህገወጥ ተግባሮች በነጻ የስልክ መስመር 9995 በመደወል ጥቆማ መስጠት እንደሚችሉ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ጨምረው ገልጸዋል።

# ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች በጣለው ዝናብ ሳይዘናጋ ክትትል እንደሚያደርግ የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ

**ፍቃዱ ዴሪሳ**

አዲስ አበባ፡-በኦሮሚያ ክልል ድርቅ በተከሰተባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በጣለው ዝናብ ሳይዘናጋ ክትትል እንደሚያደርግ የኦሮሚያ ክልል ቡሳ ጎኖፋ አስታወቀ።።

የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ምክትል ኃላፊ አቶ ገረመው ኦሊቃ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል ከተከሰተው ድርቅ በኋላ ዝናብ መጣል ቢጀምርም በድርቁ ለተጎዱ የሚደረገው ድጋፍ መቀጠል አለበት።

ከሶስት ሳምንታት ወዲህ በአንዳንድ አካባቢዎች የጣለው ዝናብ በቂ ባይሆንም በበልግ አምራች አካባቢዎች የተወሰኑ የውሃ ችግሮችና የእንስሳት ግጦሽ ችግሮችን እንደሚቀርፍ ይጠበቃል። የዝናብ ሽፋን ያላገኙ አካባቢዎችን በመለየት የሚደረገው ድጋፍ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

ከሰሞኑ የጣለው ዝናብ የድርቁን ተጽዕኖ በተወሰነ ደረጃ ይቀንሰዋል ያሉት አቶ ገረመው፤ ዝናብ ባልጣለባቸው የበልግ አብቃይ አካባቢዎች የተዘሩ ሰብሎች ዝናብ ሳይቆራረጥ ከቀጠለላቸው ከችግሩ የሚያገግሙ ቢሆንም፤ አሁንም በአካባቢዎች ክትትል እንደሚደረግ ጠቁመዋል።።

እንደ አቶ ገረመው ገለፃ፤ በድርቁ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የውሃ እጥረት የተከሰተ በመሆኑ የኦሮሚያ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ እንዲሁም ሌሎች ረጂ ተቋማት ከ125 በላይ ቦቴዎች ድርቁ በተከሰተባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በማሰማራት የውሃ አቅርቦት እንዲሰጡ ተደርጓል።።

ችግሩ ከመንግሥት አቅም በላይ መሆኑን በመገንዘብም የተለያዩ ረጂ ተቋማትን በማስተባበር ረገድ ሰፋፊ ስራዎች በመስራት ህብረተሰቡ ይህን ችግር እንዲያልፍ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል።።

በድርቁ የተጎዳው ማህበረሰብ ለከፋ ችግር እንዳይጋለጥ በክልሉ 21 ዞኖችና 19 ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም 44 በሚደርሱ በክልሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች በኩል ንቅናቄ በመፍጠር በድርቁ ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲደርስ መደረጉን ተናግረዋል።።

በ2014 በጀት ዓመት በኦሮሚያ ክልል ስምንት ዞኖች በተከሰተው ድርቅ በእንስሳት፣ በሰዎች እንዲሁም


አቶ ገረመው ኦሊቃ

በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች በፌዴራል፣ በክልል መንግሥታት እንዲሁም በሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንዲረዱ ሲደረግ መቆየቱ ተጠቁሟል።።

በዚህም እስከ አሁን ድረስ 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶች በድርቁ ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍል እንዲደርስ መደረጉንና የእህል አቅርቦቱ በማይደርስባቸው አካባቢዎች ከ77 ነጥብ አንድ ሚሊየን ብር በጥሬ ገንዘብ እንዲሰጥ መደረጉን አብራርተዋል።።

ከድርቁ ጋር በተያያዘ በእንስሳት ላይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ከተለያዩ ተቋማትና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እንዲሁም ከፌዴራሉ መንግሥት ከ651 ሺህ ሰባት መቶ በላይ ቤል (እስር) መኖ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ በማድረስ ከፍተኛ እገዛ ማድረጉን ተናግረዋል።።

ከዚህም ባሻገር ድርቁ ባልተከሰተባቸው አጎራባች ዞኖች እንዲሰማሩ በማድረግ እንስሳት በድርቁ ተጋላጭ እንዳይሆኑ በማድረግ ረገድ በርብርብ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል በተለይም በቦረና፣ ባሌና ሐረርጌ አካባቢዎች ከመቶ ሺህ በላይ ከብቶች በድርቁ ምክንያት መሞታቸውን የተናገሩት አቶ ገረመው፤ አደጋውን ለመከላከል በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ በርካታ ቁጥር ያላቸው እንስሳት ሞት መቀነስ ተችሏል ብለዋል።።

በቀጣይም ከሚገኘው ዝናብ ማህበረሰቡ ውሃ የመያዝ ሥራ እንዲያከናውንና ድርቁ በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በከፍተኛ ክትትል እየተሰራ መሆኑንም አቶ ገረመው አስታውቀዋል።

የኦሮሚያ ክልል ቡሳ ጎኖፋ በክልል ድርቅ ወይም ሌላ አደጋ ሲከሰት የአደጋ ስጋትና መከላከልን ሥራ ለመወጣት የተቋቋመ ቢሮ ነው።

## በኢትዮጵያ ተከስተው ከነበሩ ግጭቶች ጀርባ የአሸባሪው ሕወሓት እጅ መኖሩ በምርመራ መረጋገጡን ፍትሕ ሚኒስቴር ገለጸ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ተከስተው ከነበሩ ግጭቶች ጀርባ የአሸባሪው ሕወሓት እጅ እንዳለበት በምርመራ መረጋገጡን ፍትሕ ሚኒስቴር ገለጸ።

በኢትዮጵያ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች የግጭትና አለመረጋጋት ክስተቶች መስተዋላቸው ይታወቃል። በተለያዩ ምክንያቶች በተከሰቱት ግጭቶች የበርካታ ወገኖች ህይወት ሲያልፍ፤ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመትና መፈናቀልም ተከስቷል።

በእነዚህ ወንጀሎች ላይ ተሳታፊ የነበሩ አካላት በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑና ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ፍትሕ እንዲያገኙ መሰራቱን ፍትሕ ሚኒስቴር ገልጿል። የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ፍቃዱ ጸጋ፤ በተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ ግጭቶችን መንስኤ ለማጣራትና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ በተደረገው ምርመራ የአሸባሪው ሕወሓት የጥፋት እጆች መኖራቸው ተረጋግጧል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ግጭቶችን በጦር መሳሪያና በበጀት በመደገፍ እንዲሁም ስምሪት በመስጠት ስለመሳተፉ በመረጃና ማስረጃ ተረጋግጧል ነው ያሉት።“እኔ ያልመራኋት አገር መቀጠል የለባትም” ብሎ የተነሳው አሸባሪ ቡድን፤ አገር ለማፈራረስ የተለያዩ የጥፋት አማራጮች መጠቀሙን ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።

የፍትሕ ሚኒስቴር ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በቴፒ፣ በቡራዩና በአዲስ አበባ፣ በአሶሳ እና ሌሎችም አካባቢዎች የተፈፀሙ ወንጀሎች ተጣርተውና ምርመራ ተደርጎባቸው ውሳኔ እንዲያገኙ ማስቻሉንም ነው የገለጹት።

በጌዲዮና ጉጂ እንዲሁም በሀዋሳ በተፈጠሩ ግጭቶች የወንጀሉ ተሳታፊ የነበሩ አካላትም የፍርድ ውሳኔ እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

መነሻቸውን የሃይማኖትና የወሰን ጉዳይ አድርገው በቅርቡ የተከሰቱ ወንጀሎችን የሚመረምር ቡድን ወደ ስፍራው መላኩን ጠቅሰዋል። በጎንደር፣ በደባርቅና በወራቤ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ እንዲሁም በጂንካና ደራሼ ወሰንን መነሻ አድርገው የተከሰቱ ግጭቶችን በማጣራት ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል። በተለያዩ አካባቢዎች ሃይማኖትንና ብሔርን መነሻ አድርገው የተከሰቱ ግጭቶች በፌዴራል መንግሥት ብቻ እንዲታዩ መወሰኑንም ተናግረዋል።

በቀጣይም የድንበርና የወሰን ጉዳዮችን በሕጋዊ መንገድ ለመፍታት ይሰራል ብለዋል።

የጥፋት ኃይሎች አገር የማፍረስ እንቅስቃሴ አሁንም የቀጠለ ቢሆንም፤ መንግሥት ወንጀለኞችን ተጠያቂ የማድረግና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ስራ አጠናክሮ ቀጥሏል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

## ‹‹የሕግ የበላይነት ማስፈን የህልውና ጉዳይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የተለመደውን ቀና ትብብር ማድረግ አለበት ብለዋል።

የመንግሥት ትዕግስት እንደ ፍርሃት ተቆጥሮ አገሪቱ በብዙ ችግሮች እንድታልፍ ምክንያት ሆነዋል። ምንም እንኳ የሕወሓት አከርካሪ ቢመታም አሁንም በአንዳንድ አካባቢ ችግሮች እየተስተዋሉ በመሆናቸው መንግሥት የጀመረው ሕግ የማስከበር እርምጃ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ የመንግሥት ቀዳሚ ተግባር ነው። የተለያዩ ችግሮች በመፍጠር አገርን ለአደጋ ያጋለጡ ሁሉ ለህግ ለማቅረብ በትኩረት እንደሚሰራ አስታወቁ።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ባለፉት አራት ዓመታት አገሪቱ በሰላም እጦት በእጅጉ ተፈትናለች። በተለይ አሸባሪው ሕወሓት በአንድ በኩል በአገር ላይ ከፍተኛ አደጋ በመደቀን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውሸት መረጃ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ላይ እንዲዘምት አድርጓል።

የለውጡ አመራርና ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግል አሸባሪ ቡድኑን በመቅጣት አገር ለመታደግ ተችሏል። ከሕወሓት ሳይማሩ ሀገር ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ ጸረ ሰላም ኃይሎች ላይ ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያን እድገት የማይፈልጉና ጥቅማቸው የተነካባቸው ኃይሎች ከለውጡ ማግስት አንስተው የጥፋት ጎዳናን መርጠዋል። ከአሸባሪው ሕወሓት በተጨማሪ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች የብሔርና የሃይማኖት አክራሪዎችና ጽንፈኞችም አፋሳሽ እልቂት እንዲፈጠር ያላሰለሰ ጥረት ማድረጋቸውንም አስታውሰዋል።

በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ብሎም ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ የጋራ ምክክር ማድረግ የመንግሥት ጽኑ ፍላጎት ነው። ሁሉም ወገን ለብሄራዊ ምክክሩ ራሱን እንዲያዘጋጅ ጠይቀዋል።

## “የመንግሥት ዋና አላማ የሀገር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ንዋያቸውንም መልሰው ለሀገር ለማዋል ይችላሉ፤ በዚያው ልክም አካባቢያቸውን በመጥቀም የስራ ዕድሎችንም በስፋት ለመፍጠር አቅም ይኖራቸዋል ብለዋል።

በዚህ አግባብ ካየነው ከኢንተርፕራይዝ አንስቶ እስከ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች ድረስ መንግሥት የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በማሳደግ፣ በልዩነት የተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንዲሰሩ በማድረግ መንግሥት የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል ሲሉ ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

እንደ አቶ አህመድ ሽዴ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለሀብቱን ከመደገፍና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ያለው ችግር የፖሊሲ ሳይሆን ያሉትን ፖሊሲዎች በጥራት ማውረድና መፈጸም ላይ ነው።

በዚያው ልክ ባለሀብቱም ያለበትን ምርት የማሳደግ ችግሩን መቅረፍ እንዲሁም የማስፈጸም አቅም ማነስ ችግር ማስተካከል አለበት። ፋብሪካዎቹ በዘርፉ ዕውቀት ባላቸው ሰዎች እንዲመራ በማድረግና የሰው `ኃይሉን በማደራጀት የበለጠ ለማምረት መስራት ይኖርበታል ብለዋል።

## ከማዕድን ዘርፉ ተገቢውን ጥቅም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

4 ነጥብ 8 ቶን ብቻ አምርተው ለገበያ ማቅረባቸውንም ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ የዘጠኝ ወር ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ እንደገለፁት፤ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው የፀጥታ ችግር የማዕድን ዘርፉን በብርቱ እየተፈታተነው በመሆኑ የተለያዩ ኩባንያዎች እና የማዕድን አካባቢዎች ከአገልግሎት ውጪ ሆነው ቆይተዋል።

ጉዳዩ በዘላቂነት መፍትሄ የሚፈልግ እንደሆነ የገለፁት ሚኒስትሩ፤ መሥሪያ ቤታቸው በአሁኑ ጊዜ ከመከላከያ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት ኤጀንሲ እና አርቴፊሻል ኢንትሌጀንስ ተቋማት ጋር በትብብር በመሥራት ችግሩን እየቀረፈ መሆኑን አብራርተዋል።

በ14 የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ላይ የሚታይን የፀጥታ ሥጋት ለመፍታት ከፀጥታ አካላት ጋር በጥምረት መሥራቱ ውጤት እያመጣ መሆኑንም አመላክተዋል። ከዚህም ባሻገር የማዕድን ፖሊስ ዲፓርትመንት በፌዴራልና በክልሎች እንዲቋቋም ስምምነት ላይ ተደርሶ ወደ ትግበራ መግባቱንና ዲፓርትመንቶችን ለማቋቋም የሎጅስቲክስ አቅርቦት ግዢ የተጠናቀቀ መሆኑን እንዲሁም ለፀጥታ አካላት አስፈላጊው መረጃ እንዲደርሳቸው መደረጉን ኢንጅነር ታከለ ገልጸዋል።

የፀጥታ ሁኔታውን በዚህ ዓይነት አደረጃጀት ማስተካከል ከተቻለ እና ዘላቂ መፍትሄዎች ከተፈለጉለት ከዘርፉ አሁን እየተገኘ ካለው ጥቅም በላይ ማግኘት እንደሚቻል የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ በበጀት ዓመቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የወርቅ፣ የጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናት በድምሩ 458 ነጥብ 07 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል ብለዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት 6 ሺህ 947 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቧል። 2 ሺህ 317 ኪሎ ግራም የጌጣጌጥ ማዕድናት፤ 79 ቶን ታንታለም፤ 7 ሺህ 363 ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ 2 ሺህ ቶን ሶዲየም ብሮማይድ ተመርቶ ለውጭ ገበያ መቅረቡን ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

ለውጭ ገበያ ከቀረቡት ማዕድናት በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ገበያ 4 ነጥብ 6 ሚሊዮን ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ 36 ነጥብ 8 ሚሊየን ኪዩቢክ ሜትር የግንባታ ግብዓቶችም ለኢንዱስትሪዎች መቅረባቸው ተነግሯል። በሌላ በኩል 5 ሚሊየን ኩንታል የገበታ ጨው እና 588 ሺህ ኩንታል የኢንዱስትሪ ጨው ለገበያ እንዲቀርብ መደረጉን ሚኒስትሩ ባቀረቡት ሪፖርት ገልፀዋል።

በሌላ በኩል በግንባታ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ሚና ያለው የሲሚንቶ ምርት፣ የምርትም ሆነ የግብይት ሰንሰለቱ ከፍተኛ ክፍተት ይታይበታል ያሉት የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አጠቃላይ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለማምረት ካቀዱት 8 ነጥብ 2 ሚሊየን ቶን 4 ነጥብ 8 ሚሊዮን ቶን ብቻ አምርተዋል ብለዋል። ይህም ከዕቅዱ 58 በመቶ እንደሆነ አክለዋል።

የምርት ዕቅዱ እንዳይሳካ የውጭ ተፅዕኖ እንዳለበት የገለፁት ሚኒስትሩ፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የውስጥ ችግሮች በተለይም የክህሎት እጥረት እና የማኔጅመንት ችግሮች ይታይባቸዋልም ብለዋል። ፋብሪካዎቹ ከድንጋይ ከሰል እጥረት በተጨማሪ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ፣ የማምረቻ ማሽነሪዎችና የሰው ኃይል እጥረቶች እንቅፋት እንዳለባቸውም አብራርተዋል።

የማዕድን ሚኒስትሩ እንደገለፁት፤ በሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው። እንደ ድንጋይ ከሰል ያሉ ግብዓት እጥረቶችን ለመቅረፍ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የድንጋይ ከሰል ፋብሪካ ግንባታዎች ተጀምረዋል።

የግብይት ሥርዓቱን ክፍተት ለመድፈንም ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ከሲሚንቶ አምራቾች ማህበር ጋር በመቀናጀት የምርት እና የግብይት ሥርዓት መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል።ሪያው አምራች ፋብሪካዎችንና የሲሚንቶ ተጠቃሚዎችን ያለ ውጣውረድ የሚገናኙበት መደላድል የሚፈጥር መሆኑንም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## እርቃናቸውን የቀሩት የአሸባሪው ሕወሓት ውሸቶች!

ምንም ያህል ደብቆ ለማቆየት፤ ሸፍኖ ለመሸሸግ ቢሞከርም፣ ብሂሉ "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል" ነውና የተሸፈነ መገለጡ፣ የተደበቀ ይፋ መውጣቱ፣ እውነትም ሐሰትን ቦታ አስለቅቆ ከፍ ማለቱ አይቀሬ ነው። እውነትን በትዕግስት የጠበቀ፤ የተደበቀውን ሐቅ ለማወቅ ቆሻሻውን ለመግለጥ የደከመ፤ የሐሰትን ቋጥኝ ላለመሸከም የወሰነ፤ በጥቅሉ ጆሮውንም አንደበቱንም ለእውነት ያዘጋጀ ሰው ጊዜው ቢረዝምም ጨለማው ተገፍፎ ብርሃን እንደሚመጣ ሁሉ የሐሰት ክምር ተንዶ የተሸሸገው እውነት መገለጡ አይቀሬ ነው።

ይህ ጊዜ ጠብቆ የሐሰትን መጋረጃ ገልጦ እውነትን ገሃድ የሚያወጣ የዘመን ሁነት ደግሞ፤ ለዋሾዎች (እንደ ሕሊናቸው ሚዛን የሚወሰን ቢሆንም) ውርደትና ሃፍረትን፤ ለእውነት ናፋቂዎች ደግሞ አሸናፊነትና ከፍታን የሚያጎናጽፍ መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያውያን እና የአሸባሪው ሕወሓት ጉዳይም እንዲሁ ነው። አሸባሪው ቡድን ዘወትራዊ ኑሮውም ትርክቱም ሰው ሠራሽ እና የውሸት ካባን የደረበ፣ እንደውም ነጭ ውሸትን እውነት አድርጎ በማቅረብ የሚታወቅ ቡድን ነው። ኢትዮጵያውያን ደግሞ ለውሸት ኑሮና ትርክት እጅ ላለመስጠት እውነትን ፍለጋ ሲታገሉ፤ ስለ እውነት ሲሉ ከፍ ያለ ዋጋ የከፈሉ ናቸው።

የሕወሓት የጥፋት ቡድን ትናንት በተቀባባ የሐሰት ትርክት የኢትዮጵያውያንን ኅብረት ሊሸረሽር፣ አንድነታቸውን ሊንድ በርካታ ሴራዎችን አሲሯል። በአንጻሩ ለሴራ ጉዞ እጅ ያልሰጡት ኢትዮጵያውያን የአንድነት ገመዳቸውን አንስተው የሴራ መረቡን በመበጣጠስ የማይነጣጠል ገጽ ባለቤት፣ በሕብረ ብሔራዊነታቸው የተጋመዱ ሕያው ሕዝቦች የመሆናቸውን እውነት ገለጡ። ይሄም ኢትዮጵያውያንን ከፍ ሲያደርግ፤ ሕወሓትን ለውርደት ባስ ብሎም ወደ ተራ አሸባሪነት አዘቅት እንዲሽቆለቆል አስገደደው።

ይሄን እውነት መቀበል የተሳነው ሕወሓትም፣ ሕዝብን አታልሎ በሕዝብ ጉያ በመሸሸግ እሳት መለኮስ እና ሕዝብ እየተቃጠለ እሱ ለመሞቅ ራሱን አዘጋጀ። ለዚህ እኩይ ተግባሩም በሰሜን እዝ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ፈጸመ። ይሄን ጥቃት እኔ አልፈጸምኩም ሲልም ዓይኑን በጨው ታጥቦ ካደ። ሆኖም ይህ ውሸቱ ቀናትን እንኳን መግፋት አልተቻለውም።

"የምንን ምን የበላ ያስለፈልፈዋል" እንዲሉ፤ "በሰሜን ዕዝ ላይ በአርባ ደቂቃ ውስጥ መብረቃዊ ጥቃት አደረስን" ሲል ሴኮ ቱሬ የሚሉት የራሳቸው አፈ ቀላጤ በአፍ ወለምታው አማካኝነት እውነቱን አወጣው። የዚህ እውነት ገሃድ መውጣት ደግሞ ለሽብር ቡድኑ ከፍ ያለ ያለመታመን ሰብዕናውን ያጋለጠ እና የአገር ከሃዲነቱን፣ የእናት ጡት ነካሽነቱን፣ የሕዝብ ጠላትነቱት ያረጋገጠ፤ የኢትዮጵያውያንን ደግሞ እውነቱን ተገንዝቦ ለላቀ ድል የመነሳትን አቅም ያላበሰ ነበር።

የዚህ ቡድን የሽብርና የውሸት ጉዞ በዚህ አላበቃም። በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጸማቸውን እና ለወደፊቱ ከፍ ባለ መረጃ ተደግፈው የሚጋለጡ ቅጥፈቶቹ እንደተጠበቁ ሆነው፤ ከቋጥኝ በከበዱ ማስረጃዎች፣ ለዓለም በተገለጡ ሰነዶች ታግዘው የሚቀርቡ ሃቆችን ከዶ በኋላ ላይ በአፈ ቀላጤዎቹ የአፍ ወለምታ ያመነባቸውን አንድ ሁለት ማሳያዎች መጥቀሱ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፣ በወረራ ወደ አፋርና አማራ ክልል በተሰማራበት ወቅት የፈጸማቸውን እኩይ ተግባራት፤ እንዲሁም የትግራይን ወጣቶች በአፈና ይዞ ወደ ግንባር ሲያሰልፍ የቆየባቸውን እና አሁንም ይሄንኑ እያደረገ ስለመሆኑ የካደባቸው ሁነቶች በርካታ ናቸው።

በዚህ ረገድ ቡድኑ በአማራም ሆነ በአፋር ክልሎች በወረራ በቆየባቸው ጊዜያት ከተራ ሌብነት እስከተደራጀ ዘረፋና ንብረት ማውደም፤ ግለሰቦችን አፍኖ ከማሰቃየት እስከ አስገድዶ መድፈር እና ጅምላ ግድያ ሲፈጽም ሰንብቷል። ይሄ እውነት በዓይን እማኞችም፣ በሰነድ ማስረጃዎችም፣ በጥቃቱ ሰለባዎችም እንዲሁም በጥቃቱ ፈጻሚዎች ጭምር ታግዞ በተለያየ መንገድ ለሕዝብ እንዲደርስ ሆኗል። ይሁን እንጂ ይሄን በምንም ሊሸፈን የማይችል እውነት "ዓይኔን ግንባር ያድርገው አልፈጸምኩም፤ የእኔ ታጣቂዎች ጨዋና ሥነ ምግባር ያላቸው ናቸው፤..." ሲል ካደ።

በተመሳሳይ ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ የሰብዓዊ ድጋፍ ከሕዝብ ነጥቆ ለታጣቂዎች እየሰጠ ስለመሆኑ በርካቶች ቢወተውቱም፤ የትግራይን ታዳጊ ወጣቶች በግዳጅ ለጦርነት እያሰለፈ ስለመሆኑ መናገራቸውን እጃቸውን ከሚሰጡ የቡድኑ ተዋጊዎች ጭምር እየተነገረ ቢሆንም፤ ድጋፉንም ለሕዝብ እያደረሰ ስለመሆኑ፣ ወጣቶቹም በፈቃዳቸው እየዘመቱ እንደሆነ ተናገረ።

ሆኖም እውነት ስትሸፈን እንቅልፍ የማታስይዝ፤ እረፍት የማትሰጥ፣ እንዲሁ እያስለፈለፈች ለመውጣት የምትኮረኩር ናትና፤ አፉ በወለምታ በሚታወቀው የሽብር ቡድኑ ዋና አፈ ቀላጤ ጌታቸው ረዳ በኩል "አንዳንድ ከሥነምግባር ያፈነገጡ የቡድኑ ተዋጊዎች የፈጸሙት ነው" ሲል እውነቱን ተነፈሰ። የሰብዓዊ ድጋፉን በተመለከተም ሳይበላ የሚዋጋ አይኖርም ሲል ወደ እውነቱ ሲንደረደር፤ ታዳጊ ወጣቶቹንም ለሕልውናቸው መታገል የግድ ስለሚላቸው አስገድዶ ማሰለፉን አመነ።

እነዚህ ጊዜ ጠብቀው የሚወጡ የቡድኑ እውነቶች ታዲያ እንደ ዋዛ የሚታለፉ አይደሉም። ምክንያቱም ሲዋሽ በምክንያት ቢሆንም፣ እውነቱ ሲወጣ ግን በሁኔታዎች አስገዳጅነት ነው። የመዋሸቱ ምክንያት ኢትዮጵያውያንን ጥርጣሬ ውስጥ የመክተት፤ ዓለማቀፉን ማኅበረሰብ በማደናገር ሕልውናውን የማቆየት ዓላማ አድርጎ ነው።

በአንጻሩ እውነቱ ሲያመልጠው ራሱን አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባው፤ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ግልጽ እይታ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። ከሰሞኑም የያዘው ይሄው ብዥታን የመፍጠርና የማደናገር ሁነት እንደመሆኑ፤ መሰል ጊዜ የሚገልጣቸውን በሽብር ቡድኑ የታፈኑ እውነቶች በትኩረት በማጤን መራመድ ተገቢ ነው።

እፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ወደ ራስ መመልከትን እንለማመድ

**በምስጋና ፍቅሩ**

እኛ ኢትዮጵያውያን በሌሎች ሃገራት የሚደረግብን ጫና፣ ግፍ እና በደል የመሸከም አቅም የለንም። ለጠላት የመንበርከክ ታሪክም ከአባቶቻችን አልወረስንም። በሌሎች ሃገራት ሊሆኑብን፤ ሊደረጉብን የታቀዱትን ክፉ እቅዶች እንዲከሽፉ ለማድረግ በአንድነት «በቃ» የማለት አቅማችንም የሚያስገርም እንደሆነ ማንም የሚመሰክረው ጉዳይ ነው። ከእኛ አልፈን በአህጉራችን የሚገኙትን ሃገራት በተለያየ መንገድ ለመቀራመት ለሚያስቡት ምዕራባውያን ከድርጊታቸው ገሸሽ እንዲሉ የ«በቃ» እንቅስቃሴውን በአህጉሪቱ እንዲቀጣጠል በማድረግ ትልቅ አቅም መፍጠር ችለናል ብለን ኮራ ብለን ብንናገር ማጋነን አይሆንም።

ይሁን እንጂ በሃገር ውስጥ በሚገጥሙን ችግሮች በአንድ ላይ ሆኖ ለመፍታት ብሎም ለመታገል ወደ ኋላ ስንል ይስተዋላል። ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ብዙ ምሳሌዎች አነሳለሁ። በአሁን ወቅት ሃገራችን በብዙ ውስብስብ ችግሮች ተጠምዳለች። አንድ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ፤ ሌላ ጊዜ ስግብግብ ነጋዴዎች የሚፈጥሩትን ችግሮች፣ ሠዎች በማንነታቸው በጽንፈኞች ሲጠቁ ለመመልከት በቅተናል።

በተለይም አሁን አሁን ከኑሮ ውድነቱ በተጨማሪ ዛሬስ ምን ይፈጠር ይሆን? የሚለው የብዙዎች ስጋት ከሆነም ሰነባብቷል። ይባስ ብሎም አንዳንዶቹ በሌሎች ሃገራት ሲሳለቁና በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ችግር እንደሌለ ሆኖ ለማሳየት የሚያደርጉት ጥረትም ሳንወድ በግዳችን ፈገግ እንድልን ያስገድደናል።

ሌላው ነገር «እኛ ኢትዮጵያውያንን የሚያሸንፈን አንዳች ኃይል አይኖርም። » ብለን እናስባለን ወይም እናምናለን፤ ምክንያቱ ደግሞ ጠላትን ለማንበርከክ በአንድነት የመነሳት አቅም፣ ፍላጎት፣ ሞራሉና ብቃቱ ስላለን ነው። በተቃራኒው ደግሞ በገዛ ወገኑ ሹመኛም ይሁን ነጋዴ አሻጥር ሲሠራበት በአንድ ላይ ሆኖ «በቃ» ብሎ ከማጋለጥ ይልቅ «ሰው እንደሆነው እሆናለሁ» በማለት በገዛ ራሱ ላይ ሌባ ቀማኛ ሲሾም ይታያል።

ከዚህ በተጨማሪም መረጃ በመስጠት የዜግነቱን መወጣት ሲገባው እና ጉዳዩ የት አደረስከው? ብሎ ከመሞገት ይልቅ ስለ አብዛኛው ሰው ስለ ውጭ ሃገር የኑሮ ውድነት ሊተነትን ሲጣጣር ሕዝቤን ምን ነክቶት ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ከሰሞኑ ረገብ ይበል እንጂ በማኅበራዊ ሚዲያዎችም ይሁኑ በመደበኛው የመገናኛ ብዙኃን ስለ ሩሲያና ዩክሬን ጦርነት በስፋት መረጃዎች ሲሰራጩ ነበር። ይሁን እንጂ ሃገራችን ውስጥ ግን ምን እየከሰተ እንደሆነ መረጃው የሌለው ወይም እንዲኖረው የማይፈልግ ቁጥሩ ጥቂት የሚባል አይደለም።

> **ሃገራችን ኢትዮጵያ ከአግዋ መሰረዟ ይታወሳል። ይህንን ለመቃወም በርካታ የሕዝብ እንቅስቃሴ የተደረገ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፤ የሃገር ውስጥ ነጋዴ ግን በገዛ ወገኑ ላይ አሻጥር ሲሠራ እንዳላየ ታልፏል**

እርግጥ ነው የሁለቱ ሃገራት ጦርነቱ ምን አልባት ብዙ አንድምታዎች እንደሚኖሩት የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህንንም በመገንዘብ ከኢኮኖሚ አንጻርም ምን ችግር ሊያመጣ ይችላል? በሃገራችን ያሉትን ችግሮች እንዴት እንፍታቸው? መፍትሔውስ ምንድነው? ብሎ ስለ ራስ ከማሰብ ይልቅ ፤ ምንም ነገር በማይፈይዱበት እና ለውጥ በማያመጡበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ከባለቤቶቹ በላይ ነገሩን ልተንትን ማለቱ «የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች» እንደተባለችዋ ሴት መሳቂያ ነው የሚያደርገን።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከአግዋ መሰረዟ ይታወሳል። ይህንን ለመቃወም በርካታ የሕዝብ እንቅስቃሴ የተደረገ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፤ የሃገር ውስጥ ነጋዴ ግን በገዛ ወገኑ ላይ አሻጥር ሲሠራ እንዳላየ ታልፏል። ሌላም ምሳሌ እናንሳ፣ ጥቁር አሜሪካዊው የጆርጅ ፍሮይድ በዘረኝነት ምክንያት ሕይወቱ ማለፉን ተከትሎ ድርጊቱን ለማውገዝ ብዙዎች «አይካንት ብሪዝ» በማለት በማኅበራዊ ሚዲያዎቻቸውም ይሁን ባላቸውና ባገኙት አማራጭ ሁሉ ድርጊቱን ከማውገዝ አልተቆጠቡም። ዛሬ ግን በእኛ ሃገር ሰው በቁሙ ሲቃጠል፤ ሰዎች ሲፈናቀሉ፣ የሃይማኖት ተቋማት ሲቃጠሉ ስናይ ድርጊቱን ለማውገዝ መጮህ የሚገባንን ያህል አልጮህንም፤ ድርጊቱንም ማውገዝ ባለብን መጠንም አላወገዝንም ።

እንደምናስታውሰው አሸባሪው የሕውሓት ቡድን የሚያደርስባቸውን እንግልት ሸሽተው ወደ አማራ ክልል የገቡ የትግራይ ክልል ተፈናቃዮች እንዴት የእለት ጉርስ ያግኙ? ስለሚለው ጉዳይ ከማሰብ ይልቅ ስለ ሶሪያና ስለ ሌሎች ሃገራት ጉዳይ ያሳስበናል። ይህ ማለት ስለሌሎች ስደተኞችም ይሁን በጦርነት ውስጥ ስላሉት ሃገራት ተፈናቃዮች እና ችግር ስለደረሰባቸው ሰዎች ሰብዓዊነት አይሰማን ማለት አይደለም። ይልቁንም በቅድሚያ ስለራሳችን ስናስብ እና ያሉብንን ችግሮች ላይ አተኩረን ከሠራን ከራሳችን አልፈን ለብዙዎች መትረፍ እንችላለን ከሚል ከቅንነት የመጣ ሃሳብ ነው።

እናም በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን መከራ የሚወገዘውን እንደ ሰው ማውገዙ ተገቢ ቢሆንም፤ በራሳችን ችግር ላይ ግን ችግሩን ተመልክቶ ለማውገዝ ብሎም ለመተቸት እና ችግሩ እንዲፈታ የመፍትሔ አካል ስንሆን አንመለከትም። እንደውም ውጭ ላይ ሆኖ ለሚታዘብም ጉራማይሌ የሆነ ነገር ነው የገጠመን።

አንድ ሰሞን የሽንኩርት ዋጋ በከፍተኛ ዋጋ ንሮ እንደነበር ይታወሳል። አንዳንዶቹ ችግሩን ከመናገር ይልቅ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ችግሩን አሳንሰው ሲሳለቁ ለማየት ተችሏል ። ዛሬ ደግሞ ዘይትም ይሁን ሌሎች መሠረታዊ የሚባሉ የምግብ ፍጆታዎች ዋጋቸው ከዕለት ዕለት እየጨመረ በመሆኑ የኑሮ ውድነቱ ብዙዎችን እያንገዳገደ ይገኛል። በመሆኑንም በመገንዘብ መንግሥት ከሰሞንኛ ሥራዎቹ በተጨማሪ በዘላቂነት ችግሩን ለመቅረፍ መሥራት ይጠበቅበታል። ማኅበረሰቡም ሆነ ብለው የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ መሥራት ይኖርበታል።

በአጠቃላይ በውጭ ሃገራት አማካኝነት የሚደርስብንን ጫና «በቃ» ለማለት ይሁን በሌሎች ሃገራት ላይ የሚደርሱትን መከራ ግፍ እንዲያበቃ ድምጻችንን ለማሰማት እንደምንፈጥን ሁሉ ሃገራችን ውስጥ የሚከሰቱትን ሞት፣ መፈናቀል እርስ በእርስ ያለመከባበር ችግሮቻችን መፍትሔ እንዲያገኙ ፤የመፍትሔው አካል ሆኖ መሥራት ከሁላችን የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# ‹‹ጦርነት ወደገበያ የመሄድ ያህል የምናቀለው ተግባር አይደለም››

**አምባሳደር ጥሩነህ ዜና**

**የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር**



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

አስቴር ኤልያስ

**አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ቡድን ባለፉት ጊዜያት በሰውና በንብረት ላይ ያደረሰው ግድያና ውድመት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ሲዘገብ መቆየቱ ይታወቃል። ቡድኑ በዚህ ድርጊቱ ሳያበቃና ሳያፍር አሁንም በድጋሚ የጥፋት ጦሩን ለመሰበቅ እየተዘጋጀ ስለመሆኑ እየተሰማ ነው። ቀደም ሲል ያደረሰውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለመድገምም የጦርነት ነጋሪቱን እየጎሰመ ነውና በዚህ ዙሪያ ስለተፈጸመውና ሲፈጸም ስለሚችለው ሰብዓዊ መብት ጥሰትን እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ዝምታ ጋር ተያይዞ አዲስ ዘመን የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ቃለ ምልልሱን ለሰብዓዊ መብት ጥሰት ዋና ምክንያት ናቸው ከሚባሉ ጉዳዮች እንጀምር?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *ይቻላል! የሰብዓዊ መብት በተለያዩ ሃገራት በተለያዩ ምክንያቶች ይጣሳል። ነገር ግን በሁሉም ሃገራት ሊባል በሚችል ሁኔታ ጥሰቱ የሚፈጸመው በሃገሪቱ ባለው ሥርዓት ምክንያት ነው ብዬ አስባለሁ። ከሥርዓት ውጭ የፖለቲካ ባህል እንዲሁም የሕዝብ ግንዛቤ እጥረት አለ፤ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት የሚሆኑት እነዚህ ሁሉ ተደምረው ነው።*

*ደግሞም የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚፈጸመው በሁሉም ሃገሮች ነው ቢሆንም ጥሰቱ የሚፈጸመው በተለያየ ደረጃና በተለያየ ምክንያት ነው። ነገር ግን በእድገት ወደኋላ በቀሩ ሃገራት ደግሞ የበለጠ ይጎላል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ሰብዓዊ መብት ምንድን ነው? የሰው ልጆች ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? በመሪውና በሚመራው ሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት ምን መሆን አለበት? የሚሉ ጥያቄዎች ባላደጉ አካባቢዎች በግልጽ መልሳቸው የተቀመጠ አይደለም።*

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በወረራ ተቆጣጥሯቸው የነበሩ አካባቢዎች እንደነበሩ የሚታወስ ነው፤ በእነዚያ ወቅት የደረሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዴት ይገልጹታል?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *በእርግጥ ጦርነት በሚኖርበት አካባቢ ያደገ ሃገርም ይሁን ያላደገ አገር የሰብዓዊ መብት ይጠበቃል ማለት አይቻልም። ጦርነት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ መብት ጥሰት ይፈጸማል፤ ደግሞም የሰው ሕይወት ከመቅጠፍ የበለጠ ሰብዓዊ መብት ጥሰት የለም። እንደሚታወቀውም ጦርነት ሙሉ በሙሉ ሰብዓዊ መብትን አክብሮ ይሄዳል ማለት አይቻልም።*

*እንዲያም ሆኖ ግን አንዳንድ ጉልህ የሆኑ ጥሰቶችን ማስቀረት አለበት በማለት የወጡ የዓለም አቀፍ ሕጎች አሉ፤ እነዚህ ሕጎች ተዋጊ ኃይላት በተለያየ ደረጃ የሚከተሏቸው ናቸው። ነገር ግን ኢትዮጵያን ወደመሰሉ ታዳጊ ሃገራት በሚመጣበት ጊዜ እነዚያን የዓለም አቀፍንም ሆነ የሃገር ውስጥ ሕጎችን ጦርነትም እየተካሄደ ቢሆን ሙሉ በሙሉ እንኳ ባይሆን በሚቻለው ሁኔታ መጠበቅ አለባቸው ተብሎ ክትትል የሚደረግበት አካሄድ በጣም አነስተኛ ነው። ምክንያቱም በተዋጊ ኃይላት መካከል ያለው የግንዛቤ ደረጃ ራሱ በጣም አነስተኛ ነው። ስለሆነም በዚህ ምክንያት ሰብዓዊ መብት ጥሰቶቹ ከፍ ይላሉ።*

*በተለይ በሃገራችን በሰሜኑ ክፍል በተደረገ ጦርነት በውጊያው ላይ የትግራይ ክልልም በከፍተኛ ደረጃ ሚሊሻ መልምሎ ነው ወደኢትዮጵያ የላከው፤ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በሕዝብ መካከል የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ እየተካሄደ ነው። እነዚህ ሁሉ ተደምረው የሚያመጡት የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ነው። ብሎም የሚያስከትሉት የሰው ሕይወት መጥፋትን ነው። በመሆኑም በሰሜኑ አካባቢ የተፈጸመው ይህ ነው ብዬ አስባለሁ።*

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎም እንደሚያውቁት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በተለይ በሰሜኑ ክፍል የተካሄደውን ጦርነት አስመልክቶ የተለያዩ ሪፖርቶችን ሲያወጣ ነበር፤ ያቀረበውን ሪፖርት አስመልክቶ በሃገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለሪፖርቱ የተሰጠውን ምላሽ እንዴት ይገልጹታል?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *ሰብዓዊ መብት ሪፖርትን የሚመለከቱ አካላት ሐሳባቸውን የሚሰነዝሩት እንደየፖለቲካ ዝንባሌያቸው ያንን ተርጉመው ነው። የሰብዓዊ መብት ሪፖርት ለምሳሌ በምዕራባውያኑ የሚደገፉ ተቋማት፣ እነርሱ ፋይናንስ በሚያደርጉ ተቋማት፣ የእነርሱን ሐሳብና አመለካከት በሚያንጸባርቁ አካላት ተዘጋጅቶ በሚቀርብበት ጊዜ የምዕራቡ አካባቢ ሚዲያም ሆኑ መንግሥታት በአንድ ድምጽ በሚባል ሁኔታ የሚደግፉበት ሁኔታ አለ። ይህ ሄዶ ሄዶ ከፖለቲካ አተያያቸው ጋር የተያያዘ ነው።*

*ሰብዓዊ መብትን የሚገለገሉበት እንደመሣሪያ ነው። ይህ መሆን ከጀመረ ቆይቷል። ስለዚህ የፖለቲካ አመለካከታቸውንና ግንዛቤያቸውን ተከትሎ ነው የሚሄደው እንጂ በእውነት ለሰብዓዊ መብት ብለው አገሮችም ሆኑ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ድርጅቶች የሉም።*

*የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር ከመሆኔም በፊት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) በነበርኩበት ጊዜ አብሬ ሠርቻለሁ። የሰብዓዊ መብት ሕጎች በሚረቀቁበት ጊዜና የሰብዓዊ መብት ሪፖርቶች በሚቀርቡበት ጊዜ በተመድ ሳለሁ የራሴንም ሃሳብ እሰነዝር ነበር። ሕጎቹ መሬት ላይ ወርደው በሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ምን መምሰል አለባቸው የሚለውን የራሴ የሆነ አስተያየት እስጥ ነበር። ምክያቱም ሁሉም የራሱን ይዞ ነው የሚመጣ። ደግሞም ሁሉም የየራሱ እንዲጸባረቅ ነው የሚፈልገው። እኛ ዝም ብለን የሌላውን ጭራ ይዘን መከተል የለብንም። የራሳችን የሆነ ነገር መኖር አለበት ብዬ አስባለሁ። የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሆኜ በተመረጥኩበት ጊዜ የራሴን አመለካከት ማለትም ሰብዓዊ መብት በተባበሩት መንግሥታት በሚቀረጽበት ጊዜ በሥራ እንዲተረጎም ሃገራቱ እንዴት ይናገሩ እንደነበር እኔም እንዴት አድርጌ ሐሳቤን እሰነዝር እንደነበር ያንን ሁሉ አገናዝቤ ነው ስሠራ የነበረው፡*

*ይሁን እንጂ ኮሚሽነር ከመሆኔ በፊት የተባበሩት መንግሥታት በነበርኩበት ጊዜ እቸገርባቸው የነበሩ አንዳንድ ነገሮች ነበሩ፤ ለአብነት ያህል አገሮች የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሚፈጽሙበት ጊዜ የኢኮኖሚ ማዕቀብ መደረግ አለበት ይባላል፤ ነገር ግን መደረግ የሚገባው ምን አይነት የኢኮኖሚ ማዕቀብ ነው? መደረግስ ያለበት በማን ላይ ነው? የሚጣለው የኢኮኖሚ ማዕቀብ የታችኛውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚጎዳ ከሆነ ቁንጮው ላይ ያሉ አካላት በፈጸሙት ስህተት ደሃውን የበለጠ የምንጎዳ ይሆናልና እኛ ራሳችን የሰብዓዊ መብትን እየጣስን ነው ወይስ እውን የሰብዓዊ መብትን እየጠበቅን ነው? በሚል ዙሪያ ክርክር ነበር።*

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንዳሉት በአንድ ታዳጊ አገር ስልጣን ላይ ያለው አካል ባጠፋው ጥፋት የኢኮኖሚ ማዕቀቡም ሆነ ሌላ አይነት ማዕቀብ ሲጣል ይስተዋላል፤ ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው ሰብዓዊ መብት ስለተጣሰ ነው የሚል ነው፤ ይሁንና ማዕቀቡ መልሶ ሰብዓዊ መብታቸው ተጥሷል የተባሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሲጎዳ ይታያልና መብታቸው መከበሩ ምኑ ላይ ነው ይላሉ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *እንዳልኩሽ የኢኮኖሚ ማዕቀቡን በአንድ አገር ላይ መጣል የደሃውን ሕዝብ መብት መጣስ አይሆንም ወይ ስንል ባነሳነው ጥያቄ በብዙ ተከራክረን በወቅቱ ወደስምምነት መምጣት ችለናል። ስምምነቱም የነበረው ጥፋት አጥፊውን ከሕዝቡ በመለየት እርሱ ላይ መጣል የሚል ነበር።*

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ይህ እውን እየተተገበረ ነው ብለው ያስባሉ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *አዎ! ሁሌም ባይሆን አንዳንድ ጊዜ ይታያል።*

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ በአሸባሪው ቡድን አማካይነት በኢትዮጵያውያኑ ላይ በተከፈተው ጦርነት የደረሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቁጥር ስፍር እንደሌለው ጥናቶች አመላክተዋል፤ በተደጋጋሚም ሪፖርቶች ተደምጠዋልና በዓለም አቀፉ ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከተው በአሸባሪው ቡድን ላይ ጫና መፍጠር ያልቻለው ለምንድን ነው?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *ይህ ለምን ሆነ ላልሽው ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ሰብዓዊ መብት በፖለቲካ የተጠቀለለ በመሆኑ ነው። ሰብዓዊ መብት የፖለቲካ መሣሪያው በመሆኑ እነርሱን የሚደግፉትን ቡድኖች የሚጠቅም እና የሚደግፍ ከሆነ ያጎሉታል። ያ ካልሆነ ደግሞ ያጥላሉታል። በመጨረሻም ይጥሉታል።*

*ነገር ግን እነዚህ ያደጉ አገሮች እንደ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካው ቀና ቀና የሚሉና ነገም ሊሆኑ የሚችሉ አገሮች ያሰጓቸዋል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ተስፋ የሚታይባቸው አገሮችና የሕዝብ ብዛታቸውም ከመቶ ሃያ ሚሊዮን በላይ የዘለቁ አገሮች ከሌሎቹ ጋር ኅብረት ፈጥረው በአንድነት የሚነሱ ከሆነ እና በሚሊታሪም ሆነ በኢኮኖሚ በአግባቡ መደራጀት ከጀመረ አካባቢውን አስገድዶ በሚፈልጉት መንገድ ለመምራት ያስቸግራል። ይህ በመሆኑ እንዲህ አይነቱ አካሄድ አይፈለግም።*

*ስለዚህ ይህንን አውቀን አንገታችንን እንዳይዙን ምን ማድረግ አለብን በሚለው ዙሪያ እጅግ በጣም መሥራት አለብን። እነርሱ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር እርስ በእርሳችን እንድንባላ ነው እንጂ በቀጥታ መጥተው አንገታችንን አይዙም። እንድንዳከም የሚያደርጉንና እርስ በእርስ ተበላልተን እንድናልቅ የሚያደርጉት በዚህ ሁኔታ ነው። እነርሱ እንድንሆን የሚፈልጉትን ሁኔታ የሚያስፈጽሙት በሌላ ተወካይ ነው። እንደእርሱ አይነት መሣሪያ ደግሞ እንዲጠፋባቸው አይፈልጉም።*

*እንደ እኔ እንደ እኔ ለምን ቤታችን መጥተው አላጸዱልንም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ምክንያቱም ይህ በእነርሱ ዘንድ የሚፈለግ ዓይነት አካሄድ አይደለም። እነርሱም ይህን አያደርጉልንም፤ ነገር ግን የእነርሱ መሣሪያ ከሆንን ሊያስተካክሉልን ይችላሉ።*

**አዲስ ዘመን፡- እንደሚታወቀው አሸባሪው ቡድን የጦርነት ነጋሪት መጎሰም ከጀመረ ውሎ አድሯል፤ ይህ ደግሞ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት የአንበሳውን ሚና ይጫወታልና ለመከላከል መደረግ ያለበት ምንድን ነው ይላሉ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** *እውነት ለመናገር በዚህ ሁሉ የበለጠ ተጎጂ የሚሆነው የትግራይ ሕዝብ በመሆኑ እጅግ በጣም ያሳዝነኛል። ይህ ኃይል ባለፈውም ሆነ አሁን አካሄዳለሁ በሚለው ጦርነት ውስጥ ትልቁ ተጠቂ የትግራይ ሕዝብ ነው። በእርግጥ ይህ አመራር የትግራይን ሕዝብ እየጠቀመ ነው ወይ? ምናልባትም የትግራይ ወታደር የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ፈጻሚ ሊሆን*

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

ይችላል፤ በዚህ ሂደት እየተጎዳ ያለው የትግራይ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዙ መንገድ ከትግራይ ክልል ሕዝብ እጅግ የተሻለ ነው። ነገር ግን የትግራይ ክልል ሕዝብም ያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነውና ጉዳቱ ከፍ ያለ ነው። ምክንያቱም የሰብዓዊ መብት ጥሰቱን የሚያመጣው አሸባሪው ቡድን ነው እንጂ እኔ የትግራይ ክልል ሕዝብ በአሸባሪነት አልተፈረጀም።

አሁን ሌላ ትርምስ ለመፍጠር ወደጦርነት የሚንደረደሩ ከሆነ በሰው ልጅ ላይ የከፋ መከራ እንደሚደርስ አጠያያቂ አይደለም። ከመከራዎቹ ውስጥ አንዱ በርካታ የትግራይ ልጅ ማለቁ ተጠቃሽ ነው። ምክንያቱም ጦርነት ወደገበያ የመሄድ ያህል የምናቀለው ተግባር አይደለምና ነው። በኢትዮጵያ በኩል ስልጡን ወታደሮች አጥረው የያዙትን ድንበር ጥሼ ወደ ኢትዮጵያ እገባለሁ የሚለው እሳቤ የትግራይ ልጆችን ከስልጡን ወታደሮች ፊት እማግዳቸዋለሁ እንደማለት ነውና አሸባሪው ቡድን ለወታደሮቹ ምንም አይነት ርህራሄ አለመኖሩን ነው የሚያመላክተው።

እንደ እኔ የትግራይን ክልል እመራለሁ የሚል አካል ከኢትዮጵያ በኩል የሚቀርብለትን የሰላም ጥሪ ተቀብሎ በሁለቱም በኩል ያለውን ሕዝብ ሰላም እንዲያገኝ የሚደረግበት ሁኔታ ቢፈጥር ነው ደስታዬ። አንድነትን በማጠናከር ትልቋን ኢትዮጵያ ለማስቀጠል ጥረት ቢደረግ እመርጣለሁ። ሕልሜም ይህ ሲሆን፣ ለዚህ ስኬት ደግሞ እጸልያለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደሥራ መግባቱ ለሰብዓዊ መብት መከበር አስተዋጽዖው የት ድረስ ነው ብለው ያስባሉ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** በመጀመሪያ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲመጣ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ አለመከባበሩ፣ አለመተማመኑ፣ አለመግባባቱና አንዱ ሌላውን አለማዳመጡ ነው። ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ውይይት ይደረግ በሚባልበት ጊዜ በጋራ በመሆን ያሉብንን ችግሮች በጋራ እንፍታ፤ ወደ መግዳደል፣ መሰዳደብ እንዲሁም ወደአለመግባባት አንሂድ ነው። ምክንያቱም የሰው ዘር ነን፤ ደግሞም የሰለጠንን ሕዝቦች ነን ካልን በውይይት የማይፈታ ነገር የለም። ስለሆነም ችግሮቻችንን በውይይት እንፈጽም ነው መባል ያለበት።

ይህ ኮሚሽንም የተቋቋመበት መርሕ ይህ ነው። የተቋቋመው ኮሚሽን ለአንዱ ቡድን ተሟግቶ ሌላው ቡድን ተሸንፎ እንዲወጣ የሚሠራ አይደለም። ሁሉም ወገን በጥሞና ተነጋግሮና ተደማምጦ ሁሉም ወገን በአሸናፊነት የሚወጣበት መድረክ መሆን አለበት ብዬ ነው የማስበው።

ሁሉም ወገን ሲያሸንፍ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች። የኢትዮጵያ ችግር የልጆቿ አለመግባባት ነው። የልጆቿ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለመስማማት ነው። የልጆቿ በአንድነት ላይ አለመሥራት ነው። ስለዚህም ልጆቿ ተወያይተውና ተስማምተው ይህን ማድረግ ከጀመሩ ኢትዮጵያ አሸነፈች ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ የምታሸንፈው ልጆቿ ከእንግዲህ ወዲህ በጠብመንጃ አፈሙዝ መፍትሔ ለማምጣት ማቀዳቸውን አቁመው ከዚህ በኋላ ለችግሮቻችን መፍትሔ መሆን የሚችለው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ስንወያይ ነው ብለው በግልጽ መነጋገር ሲጀምሩ ነው። ኢትዮጵያ ካሸነፈች ደግሞ ሁላችንም አሸናፊ ሆንን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ነን ከሚሉት አካላት ጀምሮ አድራጊ ፈጣሪዋ አሜሪካ ጭምር የሰሜን ዕዝ ጀርባውን ከመወጋቱ አስቀድሞ በህዳሴ ግድቡ ላይ እንዲሁም መከላከያ ጥቃት ከደረሰበት በኋላም ባለው ሂደት በኢትዮጵያ ላይ እስካሁኗ ጊዜ የሚያደርሱት ጫና ቅጥ አሳጣም?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** አጥቷል እንጂ! የተመድ ሁኔታ እኔንም አስገርሞኛል። እኔ በነበርኩበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አልገጠመኝም። ይህ ሁኔታ ለአንድ ወገን ያደላ ግልጽና ገሃድ የወጣ ነው። እኔ በነበርኩበት ወቅት እስከማወቀው ድረስ የሌሎችን አመራር ተቀብሎ ወደፊት ሂድ ሲባል የሚሄድ ዓይነት ድርጅት አልነበረም። ምክንያቱም የራሱ የሆነ አቋም የነበረው ድርጅት እንደነበረ ነው የማስታውሰው። የራሱ የሆነም አመለካከት ነበረው። ስለዚህም በወቅቱ አሁን ያለው አይነት አቋም ይዞ ማየቴን አላስታውስም። ተመድ በተለይም በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ እያደረገ ያለው መድልዎ ገዝፎ የታየበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው ማለት እችላለሁ።



**በኢትዮጵያ በኩል ስልጡን ወታደሮች አጥረው የያዙትን ድንበር ጥሼ ወደ ኢትዮጵያ እገባለሁ የሚለው እሳቤ የትግራይ ልጆችን ከስልጡን ወታደሮች ፊት እማግዳቸዋለሁ እንደማለት ነውና አሸባሪው ቡድን ለወታደሮቹ ምንም አይነት ርህራሄ አለመኖሩን ነው የሚያመላክተው**

ለምን ብትይኝ፤ እንደሚታወቀው ትልቁ ኃይል አሜሪካ ነው። በአሁኑ ወቅትም በእኛ ላይ ኃይላቸውን ያሠማሩት አሜሪካና ምዕራባውያን ናቸው። የአንበሳውን ድርሻ የያዘችው ግን አሜሪካ ስለመሆኗ እውን ነው። እና አሜሪካውያን በመሩትና ባሉት መንገድ ሄደው ነው አሜሪካውያኑ ያሉትን ሐሳብ ቃል በቃል እየደገሙ በእኛ ላይ ሲፈጽሙ የነበረው። ይህን እኔ በጭራሽ ያልጠበቅኩት ጉዳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እኔ በቆየሁባቸው ስምንትና ዘጠኝ ዓመት ውስጥ በእኔም ሃገር ሆነ በሌሎች ላይ ደርሶ አላየሁም፤ አልሰማሁምም።

እኔ በነበርኩበት ጊዜ ትልቁ ነገር የነበረው የኢራቅ ጦርነት ነው። በጸጥታው ምክር ቤት ክርክር በሚደረግበት ጊዜ ሃገሬን ይመለከታል በሚል ማመልከቻ ጽፌ ነበር ስከራከር የነበረው። ምክንያቱም ሃገሬ ትልቅ ሃገር ናት። ከዚህም በላይ ራሷ ብቻ እንደ አፍሪካም የምትታይ አገር ናት። ስለሆነም መከራከሬ በዚህ አይነት ጉዳይ ድምጿዋ መሰማት አለበት የሚል እምነት ስለነበረኝ ነው። በወቅቱ የነበረው መንግሥት ተው ይህን አታድርግ ብሎ ቢለኝም፤ እኔ ግን በጸጥታው ምክር ቤት ወንበር ይገቼ እስከተቀመጥኩ ድረስ ከፈለጋችሁ አባርሩኝ በማለት ከማድረግ ወደኋላ አላልኩም። በዚያን ወቅት ታድያ እንዲህ ዓይነት ነገር ተፈጽሞ አለማየቴን ነው መናገር የምችለው።

እናም የእኛ ብቻ ሳይሆን በጸጥታው ምክር ቤትም ሆነ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ አሜሪካ ኢራቅ ላይ ጦሯን በምታሠማራበት ጊዜ በወቅቱ በአሜሪካ ላይ የደረሰው ውግዘት ከፍ ያለ ነበር። ብዙ ትችትም ነበረ። ይህ ብቻ ሳይሆን የወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ የሆኑት ሚስተር ኮፊ አናን አፍሪካን በመልካም ሁኔታ እያስጠራ የሚኖር ትልቅ ሰው ነበር፤ በወቅቱም ያለው ነገር ቢኖር ‹‹ይህ ወረራ ነው። ከወረራም በላይ የሚወገዝ ወረራ ነው›› ሲል ነበር። ይህን በማለቱ ከአሜሪካ ምን ያህል በአመለካከት ርቆ መቆሙን ያሳያል። በአሁኑ ወቅት ያለው ግን የአሜሪካንን ድምጽ የሚያስተጋባው ቃል በቃል ነው። በኮፊ አናን ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት በብዙ ክርክር የራሱን አቋም ይዞ ሲወጣ ነበር የማወቀው።

ሌላው ደግሞ አፍሪካውያኑ ራሳቸው ዝም ብለው ነበር። እኔ በማውቅበት ጊዜ የአፍሪካ ቡድን የሚባል ነገር አለ። በዚህ ቡድን ውስጥ ተሰባስበን እንወያያለን። በተለይ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ኢትዮጵያ እና ሌሎች አምስት ስድስት የሚሆኑ ሃገራት ተስማምተው ወደ ቡድኑ የሚያስተጋቡት ሐሳብና አመለካከት ቀጥታ የጸጥታውን ምክር ቤትንም ሆነ በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ጎልቶ ይንጸባረቅ ነበር። ስለዚህ የጸጥታው ምክር ቤት አባልም ባንሆን የራሳችን የሆነ ተሰሚነት እንዲኖረን እናደርግ ነበር። በአሁኑ ወቅት በተቃራኒው አፍሪካውያኑ ዝም ሲሉ ሳይ በጣም ነው ያስደነገጠኝ። ምክንያቱም ይህ እኔ የማውቀው ተመድ ነው ወይ ሌላ የሚል አመለካከት ነበር የተመላለሰብኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የተመድም ሆነ የአሜሪካ ጫና በሚበዛበት ወቅት በሁሉም አገር ያሉ ኢትዮጵያውያና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ‹‹በቃ›› የሚልና በሴላም ጉዳይ ሳይ ታላቅ ንቅናቄ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፤ይህንን የዲያስፖራውን ንቅናቄ ያዩት እንዴት ነው? መቀጠል ያለበትስ በምን መልኩ ነው ይላሉ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ወይም ዲያስፖራው የያዘው አቅጣጫና ያሰማው ድምጽ ቀደም ሲል በማብራሪያዬ ተመድ እንዲህ ሆኖ አይቼ አላውቅም እንዳልኩት አይነት ነው የሆነብኝ። ቀደም ሲል የዲያስፖራው እንቅስቃሴ ቀዝቃዛ ከመሆኑም በላይ በተቃራኒውም ይቆም እንደነበር አስታውሳለሁ። በአሁኑ ወቅት ግን ዲያስፖራው ኢትዮጵያን ደግፎ በዚህ መልኩ በታላቅ እንቅስቃሴ ሲቆም ሳይ ይህ የመጀመሪያዬ ነው ማለት እችላለሁ። ይህ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ የሚደገፍ ከመሆኑም በተጨማሪ መቀጠልም ያለበት በጎ ተግባር ነው። ኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ናቸው። ነገር ግን በዚህ መቆም የለብንም። እኛን የሚወድና ሊደገፈን የሚፈልግ ሕዝብ ብዙ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለምሳሌ እንዴት?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ጥሩ ጥያቄ! ለምሳሌ አሜሪካ ያለው ጥቁር ኢትዮጵያን የሚያየው በልዩ ሁኔታ ነው። ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያን ለመቅረብ ይፈልጋል። ከኢትዮጵያ ጋር ኅብረት ፈጥሮ ለመሥራት ይፈልጋል። እኛ ግን ለዚህ ነገር በጎ ምላሽ ስንሰጥ አንታይም።

**አዲስ ዘመን፡- ለዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** የእውቀት አለመኖር ነው፤ ራስንም ልዩ አድርጎ የማየትም ሁኔታ ነው የሚታየው። ይህ ደግሞ አይጠቅመንም። ምክንያቱም እኛ እንደምናስበው አይደለንም። መምራት የምንፈልገው አፍሪካን ነው። አውራ መሆን የምንፈልገውም በአፍሪካዊነት ነው። የእስራኤል አውራ መሆን አንችልም። ስለዚህም እስራኤላዊ መሆንን እየተመኘን የአፍሪካ አውራ መሆን አንችልም። እኔ አፍሪካዊ አይደለሁም እያልኩ አፍሪካን መምራት አልችልም። ይህ አለማወቅ ነው። በዚህ ዙሪያ ግንዛቤ ስለሌለን አርቆ ማሰብ ተስኖናል።

በነገራችን ላይ እኛ ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ በርካታ የአፍሪካ አገራት አሉ። እኛ ኢትዮጵያውያን ራሳችንን እስራኤላውያን ነን ስንል ጥቂት የማይባሉ ቀሪዎቹ አፍሪካውያን ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ይላሉ። እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ከሚሉት መካከል እነማሊ፣ ቡሩንዲ፣ ሩዋንዳ፣ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን እንኳ ለማቅረብ አልሞከርንም። ይህ በራሱ ብናውቅበት ኃይል ነበር። ኢትዮጵያ ብዙ እድል እያላት መጠቀም አልቻለችም።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት አሸባሪው ቡድን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ስለመሆኑ በተለያየ ሁኔታ ሲነገር ይደመጣልና እዚህ ላይ የሚሉት ነገር ካለ?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** እኔ እግዚአብሄር ልብ ይስጣቸው ነው የምለው። ይህ ነገር ሕዝብን ከማስጨረስ ውጪ የሚያዋጣ አይደለም። አካባቢውን የበለጠ መጉዳት ነው። ሕወሓት በዚህ አካሄዱ ከቀጠለ የበለጠ የሚጎዳው የትግራይ ሕዝብና አካባቢው ነው።

ሕዝቡ እኔን ይሰማኛል፤ ይከተለኛልም በማለት በሕዝቡ ላይ ያልተገባ ነገር መጫን ጥሩ አይደለም፤ ይህ ወንጀል ነው። ለሕዝቡ ማዘን አለባቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕወሓት የዘረጋው የሰላም እጅ አለ። ኢትዮጵያ የዘረጋችው የሰላም እጅ እንዳይታጠፍ የኢትዮጵያን መንግሥትንም ሆነ ሕዝቡን እለምናለሁ። ጊዜም ቢወስድ ኢትዮጵያ የዘረጋችው የሰላም እጅ ተቀባይነት እስኪያገኝ እንደተዘረጋ ቢቆይ እመርጣለሁ። ሕወሓትም ልብ እንዲልና የተዘረጋውን የሰላም እጅ ተቀብሎ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ሰላምና ብልጽግና አብሮነቱን ቢያሳይ እመርጣለሁ። ለዚህም ስኬት እጸልያለሁም።

**አዲስ ዘመን፡- የሁልጊዜ ተባባሪያችን አምባሳደር ከልብ እመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## በብልሃት እናስብ፤ ስለነገጋችንም ዛሬ እንዘጋጅ!

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ስንደን)**

> **ሕወሓት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሽምቅ ተዋጊዎችን አሰልጥኖ ጨርሷል። ዝግጁም ነኝ ብሏል። በትግራይ ክልል ልጁን ያላዘመተ «ሴት» ነው የሚል ዲስኩር ይዟል። እራሱም ያልዘመተ ባንዳ ነው ተብሏል። የትግራይ ጠላት ተባባሪ ነው እያሉ ወጣቱን ከአባቱ እየለዩ ሲቀሰቅሱት፣ ከፍ ሲልም ሲያስገድዱት ከርመው አሁንም የትግራይ ወጣቶች ለዳግም የጦርነት ለዳግም እልቂት እንዲዘጋጁ ገፋፍተው ምሽግ ውስጥ አስገብተዋቸዋል**

እንደምን ሰነበታችሁልኝ ውድ የአዲስ ዘመን ወዳጆቼ !! ሰነፍና አላዋቂዎች ስለትናንት፣ ብልሆች ስለአሁን፣ ሞኞች ደግሞ ስለነገ ብቻ ያወራሉ ይባላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የምንሰማቸው ዜናዎች ሁሉ የሚነግሩን ስለ ጦርነቶችና ግጭቶች በመሆናቸው የሰው ልጅ እልቂትና መፈናቀልን የኢኮኖሚ ውድቀትን የሚያስከትለውን አስከፊ ወሬ ተለማምደነው መሰል ብዙም ሳንደነቅ በቸልታ የምናልፈው ቀልድ ሆኗል።

በአገራችንም የሕወሓት «አጥፍተህ ጥፋ» ቅድመ ዝግጅት ሊጀመር እንደሆነ ሰሞኑን የሚነሰመው የሶሻል ሚዲያው ከበሮ ሲጮህም ስለተለማመድነው ቅኝቱን እየሰማን እንዳልሰማን ዝም ብለን አልፈነዋል። ሕወሓት ግን ጦርነቱን አልጨረስኩም። ያልተከፈለኝ ወይም ያልከፈልኩት እዳ አለብኝ..... ሒሳቤን አላወራረድኩም ወይም ታዝዤ ያልፈጸምኩት ተልዕኮ አለብኝ፣ ወዘተ. በማለት የጦርነት አታሞውን እየደለቀ፤ የበቀል ሰይፉን እየሳለ..... ክላሹን እየወለወለ በአውጫጭኝ የሰበሰባቸውን ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወጣቶችንና የደራጃቸውን ሚሊሻዎቹን በሽምቅ ውጊያ ሲያሰለጥን ቆይቶ አሁን በሁሉም ግንባር ለማጥቃት ተዘጋጅቻለሁ በማለት ፉከራና ቀረርቶውን እያስተጋባ፤ በትግራይ ዲጅታል ሚዲያዎች አማካኝነት ነጠላ ዜማውን ለቆ መጣሁ ቀረሁ እያለን ነው።

በቅርቡም የሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች የተባሉቱ ከክልሉ ነዋሪዎች ጋር ባደረጉት ውይይት ከመንግሥት ጋር ችግሮችን በዲፕሎማሲ ለመፍታት ሲደረግ የነበረው ጥረት አለመሳካቱን ጠቅሰው፤ የትግራይ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ለማረጋገጥ የመጨረሻ የጦርነት ምዕራፍ ላይ መደረሳቸውን ጠቅሰው ውሳኔያቸውን አሳውቀውናል። በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች የአንድ ሰው መጥፎ ሐሳብ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሕዝቦች ትልቅ እልቂት ሊሆን እንደሚችል መገመት የቻሉ አልመሰለኝም።

ለምሳሌ፣ የሕወሓቱ መሪ ዶክተር ደብረፂዮን ገ/ሚካኤል በአንድ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ያቀረቡትም ንግግር ውሀ የማይቋጥርና ለትግራይ ሕዝብ የማይመጥን መሆኑን ሳልጠቅሰው ባልፍ ደስ ባለኝ ነበረ። ነገርግን ታሪክ ነውና በሰነድ ይቀመጥ ዘንድ እንደወረደ ላቅርበው።

ዶክተር ደብረፂዮን በዚህ መድረክ ንግግራቸው «... በዚህ ሁኔታ መቀጠል አንችልም። ከሰሜን ሸዋ በኋላ ለሰላም እና ዲፕሎማሲ ዕድል ሰጥተናል። ከጦርነት በፊት እና በጦርነት ጊዜ ዕድል ሰጥተናል። ሁሉም ፖለቲካዊ ችግር በሰላም እና በዲፕሎማሲ ብቻ አያልቅም። መብታችንን ለማስከበር ሪፈረንደም ማካሄድ አለብን፤ የትግራይ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን አለበት፤» በማለት ለእነሱ የአጥፍቶ መጥፋት ተልዕኮ ሕዝብን እንደገና ጦርነት ውስጥ ለመማገድ ማነሳሳታቸው በቸልታ የማናልፈው፤ ዓለም አቀፍ ወንጀል መሆኑንም አስረግጠን ልንነግራቸው ይገባል።

በሌላ ዜና፣ የኤርትራ መንግሥት ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ የወጣው ጽሑፍ ራማ እና ባድመ አካባቢ ከሕወሓት ኃይሎች ጋር ግጭት አጋጥሞት ነበር ስለመባሉ አስተያየት ከመስጠት ቢቆጠብም፤ በድህረ ገፁ ላይ ባስተላለፈው መልዕክት በዓለም አቀፍ ሕግ የኤርትራ ሉዓላዊት ለመድፈርና ለመውረር ወያኔ በዝግጅት ላይ ይገኛል ሲል ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ እወቁልኝ ብሏል። ከቀናቶች በፊትም የአማራ ክልል አስተዳደር ከሕወሓት በኩል ሊሰነዘር ይችላል ለሚለው አዲስ ዙር ወረራን ክልሉ እራሱን መከላከል እንዲችል፣ ሕዝቡ ዝግጁ እንዲሆን ትዕዛዝ አስተላልፏል።

ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) እያንሰራራ ያለው ግጭት መቋጫ እንዲያገኝ ለሁሉም አካላት የመፍትሄ ሀሳብ ያላቸውንም ቁምነገሮች በዝርዝር ጠቅሶ አቅርቧል። ኢሰመኮ- የግጭቱ ተሳታፊዎች፣ አገር አቀፍ ተዋናዮች ሲቪክ ማህበራት፣ መገናኛ ብዙኃን፣ የሃይማኖት አባቶች እና ሌሎች አካላት ገንቢ ውይይቶችን ጨምሮ እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶችን በማደስ ግጭቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም አደራ ብሏል። ነገርግን ከጥፋታቸው ለመማር ፍላጎት የሌላቸውና ለለውጥ ያልተዘጋጁት ናፋቂ ግንቦት 20ዎቹ በእንቢ ባይነት አቋማቸው ፀንተው የትግራይን ሕዝብ ለእልቂትና ለጦርነት እንዲዘጋጅ እያስገደዱት ነው።

ምንም እንኳን ይሄን መሰል የሕወሓት ድርጊት ቢያሳዝነንም፣ ፍርዱን ለትውልድና ለታሪክ ትተን እኛ ለጋራ ነፃነታችንና ለለውጥ መዘጋጀት ይኖርብናል። በዚህ አጋጣሚ፣ የአንድ ሶሪያዊ ወጣት ታሪክ ትዝ አለኝ: : በ1943 ዓ.ም የተወለደ አንድ ሶሪያዊ ወጣት ለሚያስተምሩትና ለሚመክሩት አባቱ በ1983 ዓ.ም አንድ ደብዳቤ ፅፎ ነበር። የደብዳቤውም ይዘት እንዲህ የሚል ነበር፡-

«እስከ 1970 ዓ.ም መልካም የሆኑ ሥራዎችን እሠራ ነበር። ይሄንንም ሌትም ቀንም ነበር የምከውነው። ይህ ብቻም አይደለም፣ ሁል ጊዜም በሕይወቴ የመለወጥ ስሜት ነበረኝ፤ ለመማር የነበረኝ ልዩ ትጋት ትዝ ይለኛል። ይሁን እንጂ በ1970 ዓ.ም የምሠራቸው መልካም ሥራዎች ሁሉ ባሉበት ቆሙ። ድካምና መሰልቸት ሕይወቴን ተጫጫኑው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በማናቸውም ጊዜ ደብዳቤ ስፅፍ ዓመተ ምሕረቱን 1970 እያልኩ ነው። ዘመኑ በእኔ አቆጣጠር እስካሁን ድረስ 1970 ነው። ምክንያቱም ከ1970 በኋላ በኑሮዬ ውስጥ ምንም የተለወጠ ያደገ የተስተካከለ ነገር የለምና እባክዎት ብዙ የሚመክሩኝ አባቴ ምክርዎትን በመለገስ ወደ 1971 ያሸጋግሩኝ፤» በማለት የፃፈላቸው ነበር።

እሳቸውም ሲመልሱ፡- «መጀመሪያ አንተ ካልተለወጥክ ዘመኑም አይለወጥም፤» ብለው ነበር የመለሱለት ይባላል። በእርግጥም የአስተሳሰብ ለውጥ ያስፈልጋል። የሰው ልጅ አንዱ የስልጣኔው መገለጫው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ትግልና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ኋላ ቀር የሕይወት ዘይቤን ቀይሮ በአዲስ አስተሳሰብ በጋራ መስራትን በጋራ ማደግን አብሮነትን መለማመድ ሲጀምር ዘመኑም ወሩም ቀኑም ሰዓቱም አብሮ ይለወጣል። የአስተሳሰብ ለውጥ ስንጀምር በድህነትና በድንቁርና ላይ አምፀን የቴክኖሎጂና የኢንዱስትሪ ባህል አብዮት ማካሄድ እንጀምራለን። የአስተሳሰብ ለውጥ ስናደርግ የጎሳንና የዘር ኬላን እየጣስን ፍቅር ዘርተን ለሕዝባችን ፈጣን ለውጥ የማምጣት አቅም እንገነባለን። የአስተሳሰብ ለውጥ ስናደርግ አገራችንን በጥሩ ሁኔታ ለመለወጥ ሺህ ዕድሎች ይኖሩናል።

የአስተሳሰብ ለውጥ ብለን ስንል የበሰለና ያደገ አመለካከት፣ ሚዛናዊና አርቆ አሳቢ የፖለቲካ እውቀት ባላቸውና በተግባር በተፈተኑ የለውጥ አራማጆች የሚቀነቀን አስተሳሰብን ለአገር ፋይዳ እንዲሰጥ አድርጎ አስተማማኝ ፣ ዘላቂና ሠላም የሰፈነበት ልማትን በፅኑ መሠረት መገንባት ማለት ነው። በዚህ ዓይነት አስተሳሰባችንን ቀይረን የማንጓዝ ከሆነ እንደ ሶሪያው ወጣት ዘመኑም በእኛ አቆጣጠር እስካሁን ድረስ 1970 ሆኖ ሳይለወጥ ይቀጥላል።

የአስተሳሰብ ለውጥ ስንጀምር ግን አሁን ካለንበት የበለጠ የተሻለ፣ ደስተኛ፣ ጤናማ፣ የተትረፈረፈ፣ ስኬታማ አገር እንዲኖረን መመኜት ብቻ ሳይሆን እንዲኖረን እናደርጋለን። የአስተሳሰብ ለውጥ ስንጀምር ከመነጣጠል አብሮ መኖርን፣ አብሮ ማደግን መከባበርን... ይቅር ባይነትን ባህላችን አድርገን መለማመድና መኖር እንጀምራለን። እኛ ካልተለወጥን ግን ከዓለማችን እርቀን ከዘመን ተኳርፈን ከወገን ተጣልተን እስካለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አመተ ምህረቱን የምንቆጥረው በዚያው ክላሽን ባነሳንበት.... ደደቢት በርሀ በገባንበት ...1967 ላይ ነው የምንቆዝመው።

በመሆኑም አገርን ለመለወጥ በቅድሚያ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ ተገቢ ነው። የተለወጠ ያደገ የተስተካከለ አብሮነትን ለመቀበል ዝግጁ የማንሆን ከሆነ ሰላምን ከመስበክ ይልቅ ዘወትር የጦርነት አዋጅ ነጋሪና የእልቂት ጡሩንባ ነፊ ተብለን በታሪክ ፊት የተመፅዋችነት ካባ አጥልቀን በትውልድ የፍርድ አደባባይ መቆማችን የማይቀር ነው። እኛ ግን እንደዜጋ አገራችንን ከሽብር አደጋ ለማዳንና ሕዝባችንን ለመታደግ ምን ማደረግ ይጠበቅብናል? በማለት እራሳችንን ጠይቀን በተረጋጋና በሰከነ አዕምሮ ...ተደማምጠን መነጋገር ይኖርብናል፡፡

ሕወሓት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሽምቅ ተዋጊዎችን አሰልጥኖ ጨርሷል። ዝግጁም ነኝ ብሏል። በትግራይ ክልል ልጁን ያላዘመተ «ሴት» ነው የሚል ዲስኩር ይዟል። እራሱም ያልዘመተ ባንዳ ነው ተብሏል። የትግራይ ጠላት ተባባሪ ነው እያሉ ወጣቱን ከአባቱ እየለዩ ሲቀሰቅሱት፣ ከፍ ሲልም ሲያስገድዱት ከርመው አሁንም የትግራይ ወጣቶች ለዳግም የጦርነት ለዳግም እልቂት እንዲዘጋጁ ገፋፍተው ምሽግ ውስጥ አስገብተዋቸዋል።

ለአገራችን ችግር መፍትሔ የምንፈልግ ከሆነ ከእንዲህ ዓይነት የሕወሓት የጦርነት ዜማ ወተን ወደ ልማት መሸጋገር ይኖርብናል። በአብሮነት እንደ አገር እንድንቀጥልና ተጨማሪ ጦርነቶች እንዳይቀሰቀሱ ለማድረግ የበኩላችንን ማበርከት ይኖርብናል። መንግሥት የተናጠል የተኩስ አቁም ስምምነት ወስኖ የእርዳታ መተላለፊያ ኮሪደሮችን በመክፈት የሰላም ዋስትና የሚሆን መፍትሔ እያቀረበ ሰላም ወዳድነቱን ለዓለም ኅብረተሰብ በተግባር ከመግለፅ ያለመቆጠቡ ለዚህ ዓይነት መፍትሄ መልካም ጅምር ነው። ሆኖም ከሕወሓት እኩይ ባህሪ አንጻር ጦርነቱን ለማስቀረት ግን የሚችል አይመስለኝም።

ጦርነቱን አስቀርቶ ሂደቱን በሰላም ለመጨረስ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት ከሚታየው ጥረት በተጓዳኝ ሌላ ምን እየተደረገ እንደሆነ ለሕዝብ ግልፅ አድርጎ በይፋ ባይነግረንም፤ በሰማ በለውና በወፍ በረር እስከ ሽምግልና መኬዱን ሰምተነዋል። እውነት ከሆነም እሰየው !! ወደፊት የምናየው ይሆናል። ሕወሓት ግን አሁንም ለሰላምና ለእርቅ ዝግጁ ባለመሆኑ እጅ አልሰጥም፣ ብሎ የሽብር ጦርነቱን እንደገና ለማወጅና ሕዝብን ለማስጨረስ ቀንና ሰዓት እየመረጠ መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቃት እየተከታተለው ነው።

በእኔ እምነት ይህ ጦርነት ዳግም እንዳይቀሰቀስ መንግሥት ያለውን ትዕግስት አሟጦ የጨረሰ ይመስለኛል። ከጦርነቱ የተሻለ ሰላምን መምረጥ ትርፋማነቱ ቢያዋጣም ወያኔ ግን ከእንግዲህ ለሰላም ድርድር ለመቀመጥ ዝግጁ እንደማይሆን መንግሥት ተገንዝቦ ጦርነቱን በተመለከተ ለዓለምአቀፉ ማኅበረሰብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ አሳውቆ ሕዝቡን ከጎኑ በማሰለፍ በተጠንቀቅ መቆም ይኖርበታል። እንዳለፈው ጊዜ በቸልተኝነት የሚደረጉ መዘናጋቶች አገርና ሕዝብን ካለፈው የባሰ ዋጋ ማስከፈል ብቻ ሳይሆን እንደ አገር እንዳንቀጥል ተፅዕኖ የሚያደርጉ አያሌ ምክንያቶች አሉ። ይህ ብቻም አይደለም ትልቅ የኢኮኖሚ ውድመት አድርሰን ከፍተኛ የእርሀብ እልቂት ሊያጋጥመን እንደሚችል በመንግሥት በኩል ሊታሰብበት እንደሚገባ አሁንም... ነገም ...ከነገ ወዲያም ...በጥብቅ እያሳሰብን መወትወታችን የማይቀር ነው።

ከዚህ ባሻገር በሌሎች አውዶች በተለይ ከጦርነት ባልተናነሰ ሊጋጥመን የሚችለው ሕወሓት የሚያሰራጨው የውሸት ፕሮፓጋንዳና የሶሻል ሚዲያ ጦርነት ቀላል እንደማይሆን እርግጠኛ ሆነን በጋራ ለመመከት መነሳት፤ ኃላፊነት የሚሰማቸው የሚዲያ ተቋማት እስትራቴጂ ነድፈው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ሌላው በዲጅታል ዲፕሎማሲ የሚደረገው እሰጥ አገባ በድል ለማጠናቀቅ ዳያስፖራውን ይመለከታል። ዳያስፖራው በትልቅ በትንሹ ኩሪፊያውን ትቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲል ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ለመስራት ሎቢስቶችን በመያዝ ብሔራዊ ግዴታውን እንዲወጣ መንግሥት ግልፅነት ያለው ብሔራዊ ጥሪ ማቅረብ ይኖርበታል።

ያም ሆነ ይህ ሕወሓት ለአገራችን ችግሮች መባባስና መቀጠል ዋና ተጠያቂ ማድረግ ብቻም ሳይሆን ከበፊቱ ተሞክሯችን ልምድ በመነሳት የነበሩብንን ድክመቶቻችን አርመን መንግሥት እንደመንግሥት የተሻለ አሠራር በመዘርጋትና ለሰራዊታችን የሚደረገው ድጋፍ ከደም መስጠት ጀምሮ የተሟላ ስንቅና ትጥቅ እንዲያገኝ አብክሮ መስራት አለበት። እያንዳንዱ የመንግሥት ኃላፊ ዝግጅቱን በቀጠሮ ሳይሆን ዛሬውኑ መጀመር አለበት። በመግቢያዬ ያነሳሁት ብሂል ይሄንኑ የሚነግር እንደመሆኑ፤ ልብ ያለው ልብ ይበል። በሌላ ዝግጅት እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን። ሰላም!

# ንግድና ግብይት

# የአክሲዮን ገበያውን በጠንካራ ተቋም

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኀ ተስፋ



ዶክተር ሞላ አለማየሁ

ኢትዮጵያ በቅርቡ የሰነድ መዋእለ ንዋዮች ገበያ / የአክሲዮን ገበያ/ ታቋቁማለች። ለእዚህም ገበያውን ማቋቋም የሚያስችል ስምምነት የገንዘብ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመነት ሆልዲንግ ኤፍኤስዲ አፍሪካ ከተሰኘ ኩባንያ ጋር በቅርቡ ተፈራርመዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በስምምነቱ ወቅት እንዳሉት፤ ገበያው ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ እና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው አዲስ ዘመንን የሚያበስር ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የሆነው የሰነድ መዋእለ ነዋዮች ገበያ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የሚቋቋም ይሆናል።

በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ኢኮኖሚ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታልና ለኢንቨስትመንት የሚውሉ ተጨማሪ የረጅም ጊዜ የገንዘብ ምንጮችን እንደሚፈልግ ሚኒስትሩ ጠቁመው፤ ገበያው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ። ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለሆኑት አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ማሰባሰቢያ መድረኮችን ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መነደፉንና ለውጤታማነቱ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣም አስገንዝበዋል።

ስምምነቱን ከተፈራረሙት አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው ኢንቨስትመንት ሆልዲንጉ የመንግሥት ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ተቋም መሆኑን ጠቅሰው፣ ተቋሙ መንግሥት ስትራቴጂክ ናቸው የሚላቸውን ዘርፎች የሚመራበት መሆኑን ይገልጻሉ። ከእነዚህ ዘርፎች መካከልም ኢንቨስትመንትን ማካሄድ፣ የመንግሥት ሀብትን ማስተዳደር፣ የኮሜርሻል ሀብት የሚባሉ የልማት ተቋማትን በአንድ ላይ በመሰብሰብ በሙያ የተደገፈ አመራር በማስፈን ተቋማቱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የተቋቋመ መሆኑን ይገልጻሉ።

ገበያው በተለይ በኢትዮጵያ እየተደረገ ባለው የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ውስጥ በርካታ ዕድሎችን የሚከፍትና ለኢኮኖሚው እድገት የጎላ ሚና እንዳለው መረጃዎች ያመለክታሉ። ተቋማዊ ሥርዓት የሚበጅለትና ሕዝብ የሚተማመንበትም እንዲሆን ተደርጎ የሚቋቋም መሆኑንም ይጠቁማሉ፤ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ካናዳን የመሳሰሉ አገራት የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋት ለኢኮኖሚያቸው አጋዥ ሞተር ሆኖ ያገለገላቸው ስለመሆኑም ያመለክታሉ።

የአክሲዮን ገበያው በዋናነት ከፍተኛ የካፒታል አቅም በመፍጠር ለግሉ ዘርፍ ምጣኔ ሃብት የገንዘብ ፍሰትን በማሻሻል፣ በቀላሉ ወደ ገንዘብ ሊለወጥ የሚችል ሃብትን በመፍጠር ባለሃብቱንና ሌሎች ባለድርሻዎችን እንዲሁም ሀገርን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ፣ የገንዘብ ጉድለት ወይንም እጥረት ላለባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች አገራዊ ሃብትን በማሰባሰብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ለአገር ምጣኔ ሃብት እድገት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረውም ይታመናል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኀ ተስፋ ገበያውን አስመልክቶ ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ ሲሰጡ፣ የሰነድ መዋእለ ነዋዮች ገበያው ነጋዴዎች ገንዘባቸውን የሚያፈሱበትና ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝላቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ ግለሰቦችን ጨምሮ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የጎላ አስተዋጽኦ አለው ሲሉ ይገልጻሉ። ለዕድገት ከፍተኛ መሠረት የሚሰጥም ሲሉ ነው ገበያውን የሚገልጹት።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ገበያው ሲደራጅ በመጀመሪያ ደረጃ ኩባንያዎች ያላቸው አቅም፣ አመራር፣ አሠራር፣ ትርፍና ወጪ በሙሉ በግልጽ ይቀመጣል። ይህን ሰነድ የተመለከተ ማንኛውም ነጋዴ በሚፈልገው መጠን ሼር መግዛት ይችላል። ሁለተኛው በሀገር ውስጥ ካለው በተጨማሪ በማንኛውም አገር ያለ አንድ ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሳያወጣ ባለበት ሆኖ ሼር መግዛት ይችላል። በዚህ ፍጥነትም ገንዘቡን በውጭ ምንዛሪ ያስገባል።

በሦስተኛ ደረጃ አዲስ ሥራ ለሚጀምሩ ወጣቶች ሰፊ እድል ይዞ ይመጣል ይላሉ። ስለዚህ የሰነድ መዋእለ ነዋዮች ገበያው ኩባንያዎች በከፍተኛ ደረጃ ካፒታል ሊያሰባስቡና ቁጥራቸውን ሊያበራክቱበት የሚያስችላቸው ትልቅ አቅም መሆኑን ጠቅሰው፣ ዓለም እየሠራበት ያለ መሆኑንም ይገልጻሉ።

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ዶክተር ሞላ አለማየሁ የአክሲዮን ገበያ በኢትዮጵያ እንዲጀመር ከፍተኛ ግፊት ሲደረግና ብዙ ሲባልለት እንደነበረ ያስታውሳሉ። አሁን የመጣውን ዕድል በአግባቡ መጠቀም ሲቻልም ዘርፉ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ባለፈ ዜጎች ሃብት ማፍራት ያስችላቸዋል ይላሉ።

እንደ ዶክተር ሞላ ገለጻ፤ ገበያውን በተለይ ባለሃብቶች በከፍተኛ መጠን ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤ እያንዳንዱ ባለሃብት የአክሲዮን ገበያው በስፋት እንዲንቀሳቀስና እንዲሳለጥ በማድረግ የተሻለ ካፒታል አንዲያፈራ ያደርጋል። ግለሰቦችም በተመሳሳይ በሚገዙት አክሲዮን ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል ይፈጥራል።

በአክሲዮን ገበያ ውስጥ እንደማንኛውም ምርት አቅራቢዎችና ፈላጊዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ አክሲዮን አቅራቢው ከአክሲዮን ገዢው ጋር ተገናኝቶ እንደማንኛውም ምርት የገበያ እንቅስቃሴ በማድረግ ግብይት የሚፈጸምበት የንግድ ዓይነት እንደሆነም ያስረዳሉ።

እንደ ዶክተር ሞላ ገለጻ፤ እስከ ዛሬ የአክሲዮን ገበያው በአገሪቱ ባለመኖሩ የአክሲዮን ዋጋ አይታወቅም ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ግብይቱ በመፈቀዱ የአክሲዮን ዋጋ መታወቅ እንደሚችልና የትኛው አክሲዮን ከየትኛው የተሻለ ነው የሚለውን ጭምር የሚመልስ ሁኔታ ይኖራል። ኢትዮጵያ ውስጥ አክሲዮን እንጂ የአክሲዮን ገበያ አልነበረም። ለአብነትም አንድ ሰው ያለውን አክሲዮን ለመሸጥ ቢፈልግ አልያም አንድ አክሲዮን ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ማወቅ የሚያስችል መንገድ አልነበረም። ይህም ማለት አንድ ሰው በአንድ ባንክ ውስጥ አክሲዮን ቢኖረው ይህ አክሲዮን በዓለም ገበያ ምክንያት ምን ደረሰ የሚለውን ጥያቄ መመለስ አይቻልም። አክሲዮኑ በወቅቱ ገበያ ቢሸጥ ወይም ቢለወጥ ምን ያህል ያወጣል? ምን ትርፍ ይገኝበታል? የሚለውን ማወቅ የሚቻልበት ሁኔታ የለም።

እየተደራጀ ያለው የአክሲዮን ገበያ እንደማንኛውም ግብይት ሻጭና ገዢ የሚገናኙበት ይሆናል ያሉት ዶክተር ሞላ፣ እስካሁን ባለው ሂደት ግን አክሲዮን ከመግዛት ባለፈ ለሌላ ሲተላለፍ አልያም ሲሸጥ አልታየም ይላሉ። ለዚህ ዋናው ምክንያት የአክሲዮን ገበያ ባለመኖሩ ነው ያሉት ዶክተር ሞላ፤ በቀጣይ ግን የአክሲዮን ገበያ እንደሚኖርና ገበያው የዓለምን ሁኔታ ጭምር ያገናዘበ በመሆኑ የሚታወቅ ዋጋ ይኖራል። ዋጋው በየቀኑ፣ በየሰዓቱና በየደቂቃው የሚለዋወጥ እንደመሆኑም ይህን መሠረት በማድረግ ሻጭና ገዢ ተገናኝቶ ይገበያያል ሲሉ ያብራራሉ።

አሁን አገሪቷ ያለችበት ነባራዊ ሁኔታስ የአክሲዮን ገበያውን ተግባራዊ ለማድረግ ያስኬዳል ወይ የሚል ጥያቄ ያነሳንላቸው ዶክተር ሞላ ምላሽ ሲሰጡ በመሠረታዊነት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ካለፈው ጊዜ በተሻለ የተሟሉ ስለመሆናቸው ነው የሚናገሩት። ለእዚህም ኢትዮ ቴሌኮምን በአብነት በማንሳት ቢያንስ ዝቅተኛውን መስፈርት ማሟላት እንደተቻለ ይጠቁማሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች ማሟላትና ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ያስገነዝባሉ። በአንድ ሀገር ስቶክ ማርኬትን ወይም የአክሲዮን ገበያን ለመክፈት ሲታሰብ መንግሥትም ይሁን ሌሎች አካላት አስፈላጊና መሠረታዊ መስፈርቶችን ማሟላት የግድ እንደሚላቸው አስታውቀው፣ የአክሲዮን ገበያውን በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል የሚል እምነት እንዳላቸውም ነው የተናገሩት።

የአክሲዮን ገበያ ግለሰቦችን ተጠቃሚ ከማድረግ ባለፈ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው በጎ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው የሚሉት ዶክተር ሞላ፣ ሊወሰድ የሚገባው ጥንቃቄም እንዳለም ያስገንዝባሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የአክሲዮን ገበያ ወይም ስቶክ ማርኬት ወይም ካፒታል ገበያ ቅጽበታዊ የሆነና ከዓለም ገበያ ጋር መናበብ መቻልን የሚጠይቅ ነው። ለዚህም የተሻለ አደረጃጀት፣ መሠረት ልማትና ውጤታማ የሆነ መረጃ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለገበያው ውጤታማነት እነዚህን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላት የግድ ነው።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ጠንካራ ተቋም ከመገንባት ጀምሮ መሠረተ ልማቶችን ማሟላትና የአክሲዮን ገበያውን ሊመራ የሚችል የሰው ኃይል ማደራጀትም ያስፈልጋል። ገበያው አንዱጋ ገዝቶ ሌላው ጋ የመሸጥና የድለላ ዓይነት ሂደቶችንም የሚፈቅድ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄን ይፈልጋል። አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በተደራጀ መንገድ ካልተመራ ከታሰበለት ዓላማ ውጪ ሆኖ አገሪቷ ባልፈለገችው አቅጣጫ ሊሄድ ይችላል። ይህ ደግሞ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ይሆናል። ጠንካራ ተቋም ተገንብቶ ሂደቱን ሊቆጣጠር የሚችል የሰው ኃይል ሊኖር ይገባል ባይም ናቸው።

ገበያው እንደ ማንኛውም ንግድ ጤናማ በሆነ መንገድ መመራት እንዳለበትም አስገንዝበው፣ ከሌሎች ንግዶች በበለጠ በተሻለ ጥንቃቄና ህግ መመራት እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ። የሌሎች አገራት ተሞክሮም የሚያሳየው ይህንኑ እንደሆነ ያመለክታሉ።

የአክሲዮን ገበያ ተግባራዊ በማድረግ አገራት በብዙ እየተጠቀሙበት መሆኑንና የገበያ እንቅስቃሴው እጅግ ፈጣንና በሰከንዶች ልዩነት የሚስተዋልበት እንደሆነም የሚናገሩት ዶክተር ሞላ፣ ሚሊዮን ብሮች በሰከንድ ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉም፣ በተመሳሳይ ደግሞ ሊያጡ የሚችሉበት አጋጣሚ መኖሩን የበርካታ አገራት የአክሲዮን ገበያ ተሞክሮ ያሳያል ይላሉ። ለውጡ እጅግ ፈጣን እንደመሆኑ በቴክኖሎጂ እንዲሁም አጠቃላይ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት መረጃዎችን በፍጥነት እየተቀባበሉ መጓዝ ያስፈልጋል ብለዋል።

‹‹የአክሲዮን ገበያ በአገሪቱ እስካሁን ተግባራዊ መሆን ያልቻለው አስፈላጊነቱ ሳይታወቅ ቀርቶ ሳይሆን ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ነው›› ያሉት ዶክተር ሞላ፤ የአገሪቱ ኢኮኖሚ አክሲዮን ገበያውን መሸከም ይችላል አይችልም የሚል ጥያቄ እንደነበረም ያስታውሳሉ። ከዚህ አኳያ አሁን ባለው ሁኔታ ገበያው ተግባራዊ እንዲሆን የወሰነው አካል የሚያውቀው ነገር እንዳለ ሆኖ፤ የሚታዩ አስቻይ ሁኔታዎች አሉ ሲሉም ያብራራሉ። ለአብነትም ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ኢትዮ ቴሌኮም አሁን የደረሰበት የእድገት ደረጃ የተሻለ ሁኔታ እንዳለ የሚያመላክት እንደሆነም ይጠቅሳሉ። ሌሎች ከሰው ኃይል ጋር ያለውን ክፍተት ማሟላት ከተቻለ ከቀደመው ጊዜ በበለጠ የአክሲዮን ገበያን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዕድሎች መኖራቸውን ነው የተናገሩት።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስም የሰነድ መዋእለ ነዋዮች ገበያውን ለማቋቋም በሀገሪቱ አስቻይ ሁኔታዎች እንዳሉ በመጥቀስ የዶክተር ሞላን ሀሳብ ያጠናክራሉ። ይህ ገበያ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ ካልተጀመረ መቼም አይጀመርም ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ከዛሬ 30 ዓመት አስቀድሞ ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ይግቡ የሚለውን ሀሳብ ጨምሮ ውይይት ሲደረግ እንደነበረና አለም ባንክ፣ አይ ኤም ኤፍና የአፍሪካ ልማት ባንክ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጫና ሲያደርጉ እንደነበርና እንዳልተሞከረ አስታውሰዋል። በአሁኑ ወቅት ወደ ገበያው መግባቱ ትክክለኛ መሆኑንና ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ይልቅ ኢትዮጵያ ለገበያው ትልቅ መሠረት ያላት መሆኗንም በማስረዳት ነው ገበያው መቋቋሙን ትክክል መሆኑን ያብራሩት።

እንዲያውም ገበያው የዘገየ መሆኑን ነው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ የሚናገሩት። በሀገሪቱ ምርት ሊወጣበት የሚችል ከመቶ ሺ ኪሎሜትር በላይ መንገዶች መሠራታቸው፣ በርካታ የኃይል ማመንጫዎችና ማሰራጫዎች መገንባታቸው፣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ከዩኒቨርሲቲ በተለያየ ሙያ ሰልጥነው እየወጡ መሆናቸውና ሌሎችም በርካታ ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ በማብራራት ነው አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ያስረዱት።

እንደ ዶክተር ሞላ ገለጻ፤ የአክሲዮን ገበያ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ምክንያቱም በአግባቡና በጥንቃቄ መመራት ካልቻለ የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛ ነውና ጠንካራ ተቋም ከመገንባት ጀምሮ ከቁጥጥርና ከግብዓት መሟላት ጋር ተያይዞ በጥንቃቄ መመራት አለበት፤ ያ ካልሆነ ግን የአገሪቱን ኢኮኖሚ የበለጠ የሚጎዳው ይሆንና ከድጡ ወደ ማጡ ይሆናል። በማለት እስከዛሬ በአገሪቱ ተግባራዊ ያልሆነው የአክሲዮን ገበያ ለውጤታማነቱ በአግባቡና በጥንቃቄ መመራት አለበት። ገበያውን በአግባቡ መቆጣጠርና መምራት እየተቻለ ሲሄድ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

‹‹በአክሲዮን ግብይት ውስጥ ዋናው ተዋናይ የንግዱ ማህበረሰብ ነው›› ያሉት ዶክተር ሞላ፤ አክሲዮን የሚሸጥና የሚገዛ እንደመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ በዚህ በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄን ማድረግ፤ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ መመልከትና ልምዱን ተከትሎ መሥራት፣ ገበያው እንዴት እንደሚካሄድ መለማመድና ልምድ ማካበት እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ መንግሥት የሰነድ መዋእለ ንዋዮች ገበያውን መቆጣጠር የሚችልበት ጠንካራ ተቋም በመገንባት ገበያውን ተጠቅመው ጥፋት ሊሠሩ የሚችሉትን ሁሉ መቆጣጠር እንዳለበት ያስገንዝባሉ። ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ውስጥ የሚመደቡ ሰዎችም ዕውቀት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ፈጣን መፍትሄ ለፈጣን መንገድ

ቦጋለ አበበ

የታደሉት አገራት ፈጣን የክፍያ መንገዶችን ምኞት ማጣጣም ከጀመሩ አመታት ሳይሆን ዘመናት ተቆጥረዋል ቢባል ትንሽ የተጋነነ ሊሆን ይችላል። መቼም የፈጣኑን መንገድ ጉዳይ ትቶ የታደሉት አገራት? ማለት... ብሎ ነገረኛ ጥያቄ የሚያነሳ አይጠፋም።

ለመጻፍ የፈለኩት ግልጽ ነው፤ ኢትዮጵያ ከታደሉት አገራት ተርታ አትሰለፍም። ዕድለኛ የተሰጠውን የተፈጥሮ ጸጋና ሃብት እንዲሁም በእጁ ያለውን በአግባቡ የሚጠቀም ነው ይባላል። ኢትዮጵያ ሁሉን ተፈጥሮ ያደላት አገር ሆና ሳለ ሁሌም የታደለችውንና በእጇ ያለውን ባግባቡ መጠቀም ስላልቻለች ኋላ በመቅረቷ ዕድለ ቢስ አድርጌ ብቆጥራት ቂም እንዳትይዙብኝ በመማጸን ወደ ተነሳሁበት የፈጣን የክፍያ መንገዶች ጉዳይ ልመለስ።

ፈጣን የክፍያ መንገድ እጅግ ምቹ፣ የትራፊክ መጨናነቅ ፈፅሞ የማይታይበት፣ በተፈለገውና በተፈቀደው የፍጥነት ገደብ አሽከርካሪ ቢጓዝበት መልካም መሆኑን መንገር ለቀባሪ ማርዳት ይሆናል። ኢትዮጵያ ከታደለው ዓለም ዘግይታም ቢሆን በጣት ከሚቆጠሩ አመታት ወዲህ የፈጣን ክፍያ መንገድን ጣዕም በትንሹም ቢሆን ቀምሳለች። ማጣጣም ግን ይቀራታል። መቼም የዚህን መንገድ ምቾት ለመመስከር በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን መጓዝ አይጠይቅም። ለቅምሻም ቢሆን ከአዲስ አበባ አዳማ ወይም ከአዲስ አበባ ቢሾፍቱ ከመቶ ያልበለጠ ኪሎ ሜትር መጓዝ ስለመንገዱ ትንሽም ቢሆን ሃሳብ ለመሰንዘር በቂ ይመስለኛል።

ታዲያ ይህ መንገድ ምን ምቹ ቢሆን በድንገት አደጋ እንዲከሰት የሚያደርጉ እንቅፋቶችና በርካታ የሕይወትም ሆነ የንብረት ውድመትን የሚያስከትሉ ችግሮች እየተስተዋሉበት እንደሆነ ምስጢር አይደለም። ዘንግተን ካልሆነ በቀር አንድ ሙሉ ሚኒባስ ሰው በዚሁ መንገድ ላይ ወጥቶ የቀረበት ዘግናኝ የትራፊክ አደጋ የሚረሳ አይደለም። የዚህ ፈጣን መንገድ ፍላጎትና ተጠቃሚ በእጅጉ እያደገ ስለመምጣቱ የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ በየጊዜው ከተጠቃሚዎች ሰበሰብኩት ብሎ የሚነግረን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ይገልጥልናል። ለዚህም ነው መሰል ከአዲስ አበባ ሐዋሳ የሚዘልቅ ተጨማሪ ፈጣን የክፍያ መንገድን ምቾት እንድናጣጥም በቅርቡ ተመርቆልናል።

በእርግጥ ይህ መንገድ ገና በመሠራት ላይ ያለ ቢሆንም ከአዲስ አበባ እስከ ባቱ ያለው ብቻ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ከቅርብ ወራት ወዲህ ክፍት ሆኗል። ይህ እስከ ሐዋሳና ከዚያም አልፎ ረጅም ርቀት አቋርጦ እንደሚዘረጋ የሚነገርለት መንገድ ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ እስከሚገኝበት ከተማ ድረስ ለአገርና ሕዝብ እያበረከተ ያለውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም የተጠቀመው ያውቀዋል። ይህን መድገሙም አንባቢን ማሰልቸት ነው። ከጥቅሙ ጎን ለጎን እያጎደለ ያለው ነገር ግን እያየን ያላየን አይተንም ያላስተዋልነውን እንድናጤን ይረዳል።

በእርግጥ በዚህ መንገድ የሚስተዋሉ ነገሮች ቀደም ብሎ ከተሠራው የአዲስ አበባ አዳማ ፈጣን መንገድ የተለዩ አይደሉም። የተለዩ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር ግን በንብረትና በተለያዩ የዱርና የቤት እንስሳት ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ነው። መንገዱን ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የመጠቀም ልማዱም በዚሁ መስመር ጎልቶ እየታየ ስለመምጣቱ እግር ጥሎት ወደ ስምጥ ሸለቆዎቹ ከተሞቻችን የተጓዘ አይጠፋውም።

በዚህ የፈጣን መንገድ መስመር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ እንደ ጥይት እየተተኮሱ በሚበሩ ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ውስጥ ገብቶ የትኛውም ነብስ ያለው ነገር በራሱም ይሁን በሌሎች ላይ አደጋ እንዳያስከስት የተለመደ የሽቦ አጥር ታጥሮ ይገኛል። ይህን አጥር እንዲህ ለማለት በማይቻል መልኩ አልፈው የሚገቡ የቤትና የዱር እንስሳት አልፎ አልፎ ሰዎች የአደጋው መንስኤ ናቸው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ችግርና አደጋ ሲከሰት ጥፋተኛው ማን ነው? ማነው ተጠያቂው? ሾፌሩ ነው ወይስ ሌላ? ወይስ የክፍያ መንገዶች ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት?። ጥፋቱን በአንድ ወገን ላይ ብቻ ማላከክ ፍትሐዊ አያደርግም። ሁሉም ወገን ለዚህ ችግር የራሱ ድርሻ አለው። የፈጣን መንገዱ ውስጥ ሰውም ይሁን እንስሳት ድንገት ገብተው አደጋ እንዳይፈጠር የሽቦ አጥር የተሠራ ቢሆንም ይህን አጥር በየቦታው በማፍረስ ወይም ቀዳዳ በማበጀት በየመንገዱ ሰዎችና እንስሳት እንዲሁም ንብረት ላይ ለሚከሰቱ አደጋዎች መቼም እንስሳቱን ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም። መንገዱ አቋርጦ በሚያልፍባቸው አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ እንደአጠቃላይ የዚህ ችግር መንስኤ ባይሆንም ጥቂት ግለሰቦች በየመንገዱ ጥግ ለከብቶች ግጦሽ ሲሉ የሽቦውን አጥር በማፍረስ ወይም እንስሳቱን ወደ መንገዱ ሲያስገቡ ይታያል።

መንገዱ ከክፍያ መንገድ መግቢያ እስከ መውጫ ድረስ እንኳን ሁለት ተቀራራቢና አብሮ ነዋሪ ጎረቤታሞችን የለየ እንደመሆኑ መጠን፣ ሁለቱ ግራና ቀኝ ያሉ ተጎራባች የነባር ቀዬዎቹ ባለቤቶች እንደ ልብ መንገዱን ተሻግረው ቡና ባይጠጡ እንኳን ለችግር መደራረስና መጠያየቅ የሚችሉ አይመስለኝም።

ችግሩ እንግዲህ ቀደም ብሎ የተከሰተ ቢመስለኝም እንስሳቱ እየገቡ ያሉት ምናልባት መንደርተኞቹ በቀደዱት አጥር፣ ወይም መጠገን ሲገባው ትኩረት ባልተሰጠውና ባልተጠገነው አጥር ዘለው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

ጉዳዩ አሳሳቢ የመሆኑን ያህል አፋጣኝ መፍትሔ ያሻዋል ብል ማጋነን እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ምነው የአገራችን ትራፊክ ፖሊስ ፈጣን መንገድ መግቢያው ላይ በመሆን በርካታ ሾፌሮችን በጥፋተኝነት ሲቀጡ ይውላሉ፣ ያመሻሉ። ቅጣቱስ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን እነዚህ ትራፊክ ፖሊስ የመንገዱን አደገኛነት፣ ሊከሰሱና በደንብ መተላለፍ ምክንያት ሊቀጡ የማይችሉ እንስሳትን ችግር ለበላይ ኃላፊዎቻቸው ሳይታክቱ ምን ያህል አመልክተው፣ የውሳኔ ሐሳብስ አሰጥተዋል የሚለውን ለእነሱ እንተወው።

መንገዱን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የክፍያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ በመንገዱ የውጭ ግራና ቀኝ በኩል ያለውን የሽቦ አጥር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት ሰጥቶት ቢያስጠግን የመፍትሔ አካል ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ፈጣን የክፍያ መንገዱ ሲሠራ በመንገዱ ግራና ቀኝ በኩል የሚገኙ ነዋሪዎችን እንደ ልብ የማያጠያይቅና የአካባቢው ማኅበረሰብ ችግር ፈቺ አለመሆኑ በጥናት ከተረጋገጠ፣ ቢቻል በተወሰነ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከአዲስ አበባ መውጫው ላይ ቃሊቲ አካባቢና ሌሎችም መንገዶች ላይ እንደተሠሩት ድልድዮች ቢሠሩ የመፍትሄ አካል ሊሆን ይችላል።

በፈጣን መንገዱ ላይ ሰዎችንና የተለያዩ የቁም ከብቶችን ማየት እየተለመደ ቢመጣም አንድ ቦታ መቆም አለበት። እነዚህ እንስሳት በፍጥነት መንገዱ የቀን ተቀን እንቅስቃሴ ላይ እክል ፈጣሪዎች በመሆናቸው፣ የእነዚህ እንስሳትና ተሽከርካሪ ባለቤትና የክፍያ መንገዶች ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በጋራ ሆነው ወይም በተናጠል ድርሻቸውን ቢወጡ፣ እንደ ቀልድ የሚጠፋውን ሕይወትና ንብረት መታደግ ይችላሉና ቢታሰብበት።

# ዓለም አቀፍ

## «ቻይና ታይዋንን በኃይል ለመያዝ ከሞከረች አሜሪካ ወታደራዊ ኃይሏን ትጠቀማለች»

-ፕሬዚዳንት ባይደን



አዲስ አበባ፡- ግንቦት 15፣ 2014 (ኤፍ ቢ ሲ) ቻይና የታይዋን ደሴትን በኃይል ለመያዝ ከሞከረች አሜሪካ በቀጥታ ከቻይና ጋር ግጭት ውስጥ ለመግባት ዝግጁ መሆኗን የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስታወቁ።

ጆ ባይደን ከጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ ጋር በቶኪዮ ተገናኝተው በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት፣ ዋሽንግተን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘችው በቻይና እና በታይዋን መካከል በሚፈጠር ግጭት ውስጥ ታይዋንን ለመከላከል በቀጥታ ወታደራዊ ኃይሏን ልታሰማራ ትችላለች።

«እኛ የቻይናን ሉዓላዊነት እናከብራለን፤ ነገር ግን ቻይና ታይዋንን በኃይል የመያዝ ስልጣን የላትም ይህንን አንታገስም » ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን።

በእስያ ምድር የመጀመሪያውን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት በማድረግ ላይ የሚገኙት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፣ ጉብኝቱ በክፍለ ዘመኑ የመጀመሪያው ቻይናን ያላካተተ ጉብኝት ነው ተብሏል።

የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ እና የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባይደን ቻይናን እንዴት እንከላከል በሚል ርዕሰ ጉዳይ ዙርያም ሳይመክሩ እንዳልቀሩ ኒኬ ኤዥያ የተባለን የዜና ምንጭ ጠቅሶ አርቲ ዘግቧል።

በውይይቱ ላይ ከሁለቱ መሪዎች በተጨማሪ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን፣ የንግድ ሚኒስትር ጂና ሬይሞንዶ፣ የንግድ ተወካይ ካትሪን ታይ፣ በጃፓን የአሜሪካ አምባሳደር ራህም አማኑኤል እና የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ጃክ ሱሊቫን መገኘታቸው በዘገባው ተጠቅሷል።

ቻይና በአሁኑ ጊዜ ሰራዊቷን ወደ ታይዋን እያስጠጋች በማስፈር ላይ መሆኗ «ቻይና ሰራዊቷን በማስገባት ታይዋንን ልትወር ነው» የሚል ከፍ ያለ ስጋት እንዳለባትም ነው ባይደን በንግግራቸው የጠቆሙት።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከዚህ ቀደም ባደረጉት ንግግር፣ ዋሽንግተን የቻይናን «የአንድ ቻይና» ፖሊሲን እንደሚያከብር ነበር የገለጹት – ይህም ቤጂንግ በሚገኘው ማዕከላዊ መንግሥት ለምትመራ ለአንድ ቻይና እውቅና የሚሰጥ ንግግር ተደርጎ ነበር የተወሰደው።

ዛሬ ደግሞ ታይዋንን ለመከላከል ስንል ከቻይና ጋር ለመዋጋት ዝግጁ ነን ሲሉ ተደምጠዋል ባይደን።

ቻይና በበኩሏ፣ በሉዓላዊነቴ እና በግዛት አንድነቴ ላይ ለመደራደር ቦታ የለኝም ብላለች።

ዋሽንግተን የቻይናን ሕዝበ ውሳኔ አቅልላ ልታይ እንደማይገባ በማስጠንቀቅ ግዛቷን ለመጠበቅ ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎች እንደምትወስድ የቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ዋንግ ዌንቢን ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ቃል አቀባይ ዋንግ ዌንቢን ይህንን ያሉት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን «አስፈላጊ ከሆነ ታይዋንን ለመከላከል ወታደራዊ ኃይል እንጠቀማለን» ማለታቸውን ተከትሎ ከሰዓታት በኋላ ነው።

አሜሪካ በቤጂንግ የምትመራ ታይዋን የምትባል አንድ የቻይና ግዛት እንዳለች የሚያስገነዝበውን የ«አንድ ቻይና ፖሊሲን» እንድታከብር ቻይና በድጋሜ ጠይቃለች።



## «በዩክሬን የጸጥታና ደኅንነት ጉዳይ ላይ ሩሲያ ከማንም ጋር ለውይይት አልተቀመጠችም»

ሰርጌ ላቭሮቭ

አዲስ አበባ፡- በዩክሬን የጸጥታና ደኅንነት ጉዳይ ላይ ሩሲያ ከየትኛውም አገር ጋር ለውይይት እንዳልተቀመጠች የአገሪቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ተናገሩ።

ሰርጌ ላቭሮቭ ከካዛኪስታን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሙክታር ትሌበርዲ ጋር ተወያይተዋል።

ከውይይቱ በኋላ ከጋዜጠኞች ጋር በነበራቸው ቆይታ፣ በአሁኑ ጊዜ የሩሲያ ከፍተኛ ዲፕሎማቶች የዩክሬንን ጸጥታና ደኅንነት በተመለከተ ከየትኛውም አገር ጋር ለውይይት እንዳልተቀመጡ ጠቁመዋል።

ከአምስት ቀናት በፊትም ለዩክሬን ላቀረብነው የሥምምነት ቅድመ ሁኔታ እና የእነርሱን አስተያየት የያዘ ምላሽ አልደረሰንም ብለዋል።

ሰርጌ ላቭሮቭ ይህን ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠታቸው በፊት ነው የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ በፖርቹጋሉ ፓርላማ ላይ በበይነ-መረብ ቀርበው ዓለምአቀፍ አጋር አገራት የከባድ መሣሪያዎች ድጋፍ ማቅረባቸውን እንዲቀጥሉ ነው ያሳሰቡት።

በሌላ መድረክ ዜሌንስኪ፣ ዩክሬን በሩሲያ በተከፈተባት ጦር ኢኮኖሚዋ በመጎዳቱ 7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያስፈልጋታል ሲሉ ለዓለም ባንክና ለዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም አመራሮች መናገራቸውን ሲጂቲ ኤን ዘግቧል።

እስካሁን 7 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዩክሬናውያን ከቀያቸው ሲፈናቀሉ፣ 5 ሚሊዮን ያህል ዩክሬናውያን ደግሞ አገራቸውን ጥለው ወደ ሌሎች አገራት ተሰደዋል።

# ባለውለታዎቻችን

# ፍሬያማው ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው

**ግርማ መንግሥቴ**

ሸማ በየፈርጁ . . . እንዲሉ ባለ ውለታነትም እንደዛው ነው፤ በየዘርፉ፣ በየፈርጁ ... ውለታ አለ። በመሆኑም ይህ ዓምድ በእስከ ዛሬ ጉዞው ባለውለታዎችን ከየፈርጁ ሲያመጣ ሲዘክራቸው፤ ለትውልድም ሲያስተላልፋቸው የቆየው። ከጦር ሜዳ እስከ ሕክምናው፤ ከሳይንቲስቱ እስከ ነጋዴው፤ ከሠዓሊው እስከ ሥነጽሑፍ ባለሙያው ወዘተርፈ ድረስ ዘልቆ ባለውለታዎቹን ወደ አሁኑ ዘመን ብቅ አድርጓል። ይህ ደግሞ፣ ጀግናን ማወደስ፣ ባለውለታን ማስታወስ ግድና ኃላፊነትም ስለሆነ፣ ወደ ፊትም የሚቀጥል ይሆናል።

የዛሬውም ልክ እንደ እስከ ዛሬዎቹ ሁሉ ተመሳሳይ ሲሆን፤ ተመሳሳይነቱም ባለውለታን ማስታወስና ሕይወትና ሥራዎቹን መቃኘት ነው።

በዚሁ መሠረትም ወደ ሥነጽሑፉ ዓለም ጎራ በማለት በዚሁ ዘርፍ ለአገር፤ በተለይም ለዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋፅዖ፤ በገደምዳሜውም ቢሆን "ሕይወታቸውን"ና ተሞክሯቸውን እንቃኛለን።

ዛሬ በእዚህ ዓምዳችን የምንዘክራቸው ባለውለታ የመጀመሪያው የፎክሎር ተመራቂና መምህር፣ ተመራማሪ፣ ሃያሲና ባለቅኔ፣ ሰባት ቋንቋዎችን ይናገሩ የነበሩ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ናቸው። ባለ ውለታነታቸው ድንበር የለውም፤ በተለይ በሙያ ዘርፋቸው፤ በጥናትና ምርምር መስካቸው ያለ ምንም ወደ ኋላ ማፈግፈግ ያላቸውን ሲቸሩ የኖሩ ስለመሆናቸው የሚያውቋቸው ሁሉ ይናገራሉ። ይህ ጸሐፊም በተወሰነ መልኩ፣ በሚያውቃቸው ልክ ይህንን አስተያየት ይጋራል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ መምህርነት ለረጅም ዓመታት ያገለገሉት ገጣሚ፤ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፤ ተወዳጅ መምህር፤ በሥነ- ግጥም አጻጻፋቸው ለየት ያሉ መሆናቸው የተመሰከረላቸው ናቸው።


ይህንን የሰይፉን ልዩ ችሎታና ለየት ያለ የአገጣጠም ብልሀት (ብርሀኑ "አፈንጋጭነት" ይለዋል) በተግባር ለማረጋገጥ ከተፈለገ ብርሃኑ ገበየሁ በአዘጋጀውና በአገራችን በአይነትና አቀራረቡ "አዲስ" መሆኑ በተነገረለት "የአማርኛ ሥነ ግጥም" መጽሐፍ (በተለይም ከገፅ 41 እስከ 48 ድረስ ባለው) ውስጥ አጥኚው የተነተነውን የገጣሚውን ሥራ፤ እንዲሁም፣ በድሉ ዋቅጅራ "በሥነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር" (1996 ዓ.ም) ገጽ 72 ላይ ከሰይፉ ሥራዎች አንዱና ምናልባትም ከአሁኑ ዘመን ሞጋች ሥራዎች መካከል አንዱ የሆነውን "የተኳጎጠ ልብ"ን የፊት ሽፋን በመውሰድ እንዴት በመጽሐፉ ይዘት ለተነሳው ዓላማና ይዘት ማጎልበቻነት እንዴት እንደ ተጠቀመበት መመልከት ይቻላል።

የሰይፉ መታፈሪያ ፍሬውን በ 88 ዓመታቸው፣ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ተከትሎ በጀርመን ሃንቡርግ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ እና የኢትዮጵያ ጥናቶች የትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ጌቲ ገላዬ እና ሌሎች የቀድሞ ተማሪዎቻቸው በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች እንደተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬውን "መምህር" ወይም "ሰር" ወይም "ጋሼ" አልነበረም የሚሏቸው። የሚሏቸው "አብዬ ሰይፉ" ነበር።

በ1983 ዓ.ም ስልጣን ላይ የወጣው ኢሕአዴግ ካባረራቸው 42 አንጋፋ ምሑራን መካከል አንዱ በነበሩትና ለስደትም ከተዳረጉት ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ከተማሩት አንዱ የዶቼ ቬለው ጋዜጠኛ ነጋሽ መሐመድም በዶቼ ቬሌ ጣቢያ እንደተናገሩት የሰይፉ መታፈሪያን የአስተማሪነት ለዛና ብቃት አውርቶ መጨረስ አይቻልም፤ የሚጠገብም አይደለም። ነጋሽ "ሰይፉ" ይላል በፈገግታ፤ "አብዬ ሰይፉ ነበር የምንላቸው። ብቻ 'አብዬ' ያልዋቸው ከኛ ቀደም ብሎ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው።" ይላል። ሲቀጥልም "ሰይፉ መታፈሪያ እንደ አስተማሪ፣ እንደ ጓደኛ፣ እንደ አባት ነበሩ" ሲልም ነው የሚያስታውሳቸው።

በሐረር ልዑል ራስ መኮንን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፤ በአቴና ዩኒቨርሲቲ (ነገረ መለኮት)፣ በፓሪስ - ሶርቦን (እስልምና-ነክ) ትምህርት መከታተላቸው ለሥራዎቻቸው ስኬታማነት እጅጉን እንደጠቀማቸው ይነገርላቸዋል።

በዘርፉ "ቁንጮ" ሊባሉ የሚገባቸው፣ ስድስት የታተሙ፤ እና ሦስት ያልታተሙ የግጥም መድበሎች አሏቸው፤ ረጃጅም መጣጥፎችንና በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎችን ያበረከቱት ሰይፉ የተዋጣላቸው ሃያሲም ናቸው። ይህንን የሃያሲነት ሙያቸውን በአንድ ወቅት ስለ ገብረክርስቶስ "ገብረክርስቶስ ገጣሚው" በሚል ርዕስ ባስነበቡት ጽሑፍ መመልከት የሚቻል ሲሆን፤ እንዲህ ብለውለት ነበር፤



**ሰይፉ መታፈሪያ**

"ገብረክርስቶስን የማውቀው ከሐረር ትምህርት ቤቱ ጀምሬ ነው"። እዚያ ባዶ እግራችንን፣ በቴኒስ ኩዋስ ተጫውተናል። ገብረክርስቶስ፣ የእግር ጣቶቹ እኩል ስለሆኑ፣ ኳሱን የሚመታው በእግር ኩርኩም ነበር – ኹሌ የከረረች ምት።

ከእለታት ባንዱ ቀን ግን፣ ዕረፍት ወጥተን፣ ግማሹ በሚሯሯጥበት፣ ግማሹም ኳስ በሚጫወትበት ሁኔታ ውስጥ፣ ገብረክርስቶስ ጥጋት ተቀምጦ፣ ቁም"ጣ ሱሪውን አጋልጦ ባዶ ጭኑ ላይ ሥዕል ሲሠራ እንዳየሁት አስታውሳለሁ። እና አሁን መለስ ብዬ ሳስብ ሥዕል ምንኛ ከልጅነቱ ከጭንቅላቱ ገብቶ ኖሯል እላለሁ። ለዚህም የአባቱ የአለቃ ደስታ ነገዎ የድጉሥ፣ የቁም ጽሕፈትና የብራና መጻሕፍት ላይ ሥዕል ምን ያኽል ተፅዕኖ አድርጎበት ነበር ይሆን? በምንስ መንገድ? እላለሁ።

ያ እንዳለ ሆኖ ግን፣ ገብረክርስቶስን እዚህ እማንቀራብጥ በሠዓሊነቱ ሳይሆን በገጣሚነቱ ነው።

የገብረ ክርስቶስን ግጥሞች አንዴ ወጥቻቸው የግጥም መድበል መጽሐፉን ("መንገድ ስጡኝ ሰፊ" 1998 ዓ.ም) እንዳጠፍኩ፣ ገብረክርስቶስ ባሳብ አካቶው ምንኛ አይጠገቤ ነው። በእይታ ስንዘራውም ምንኛ አራዝሜ ነው፤ በሌላ ምንኛ ... ምንኛ ... ምንኛ አልኩ።" በ"አሰነኛኘት" ንዑስ ርዕስ ስርም "ገብረክርስቶስ ደስታ፣ ዘጠና በመቶውን ወል ግጥም ገጣሚ ነው።" በማለት የገብሬን ሥራዎች በይነዋል። (የአብዬ ሰይፉን የሂስ አቅምና የሃያሲነት ብቃት በሚገባ ለመገንዘብ ሙሉ ጽሑፉን (ድረ-ገፅ ላይ አለ) ማንበቡ ጠቃሚ ነው።

ስለ ከበደ ሚካኤልም "በስንኝ-አጠፍ ስንኝ" ንዑስ ርዕስ ስር "ስንኝ – አጠፍ፣ አንዱን ሙሉ ውል ስንኝ ከሁለት ግጥማዊ ወይም ስንኛዊ እኩሌታ፣ ወይም ወል ገጽታውን ከማያሳጣ ቦታ ማጠፍ ነው። የስንኝ-አጠፍ ስንኝ – ምናልባት – የመጀመሪያው ተጠቃሚ ከበደ ሚካኤል ናቸው።"

**ሰይፉና ኢትዮጵያ ምን እና ምን ናቸው?**

ሁለቱ የሚለያዩ አይደሉም። አንድ ናቸው ማለት ይቻላል። ለዚህ አስተያየታችን መነሻችን ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈራረቀ ሕዝብና አገር የሚያተራምሰውን፣ በቆሸሸ አስተዳደር የተሞላውን፣ በፀረ-ዲሞክራሲነት የታበየውን ... የኢትዮጵያ ሥርዓትና መንግሥታቱን በሚሸነቁጡበት "የተኳጎጠ ልብ" መድበል ከ"ብእሮጋዊ መግቢያ" ባለው ገጽ በ"አበርክቶት" ርዕስ ያሰፈሩት ግጥም ሲሆን፤ እሱም፡-

**ለናት ኢትዮጵያ**
**ሳገሬ**
**ሕዝባዊት ማኅደሬ**
**. .**
**ለሱዋ አንድነት**
**ነፃነት**
**የዘራይነቱዋ ኩራት።**
**. .**
**ለዘላለም ተገኝቶቱዋ**
**ብሔር ጥናቱዋ**
**እናት ጥሬቱዋ።**
**. .**
**ለድል ብርታቱዋ**
**በየተሰለፈችበት**
**ያፍሪካ ጌጥ ነቱዋ።**
**. .**
**ለሱዋ ይሁን**
**ይሄ አበርክቶ**
**ከኔ**
**ለኔ - 'ናት**
**ለኔ - 'መቤት**
**በርከክ ብዬ እነሆሽ እምሳት።**

ሰይፉ መታፈሪያ በጠንካራ ሠራተኛነቱና ባበረከታቸው ሥራዎቹ ብቻ የሚለካ ምሑር ሳይሆን ለተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ ማስተማሪያ ቴክስቶች ወዘተ በግብዓትነት ማገልገሉ በራሱ አንድ ትልቅ ውለታ ነውና በዚህም ሊነሳ፣ ሊታወስና በባለውለተኛነት ሊወደስ ይገባዋል። በተለይ ለሙያ ዘርፉ ካበረከተው አስተዋፅኦ አኳያ ከላይ የጠቀስነውን የብርሃኑን መጽሐፍ ወስዶ በምሳሌነት መመልከት ይቻላል።

ብርሀኑ ገበየሁ ከአስር ዓመት በላይ በፈጀ መጽሐፉ ዝግጅት ወቅት ይሁነኝ ብሎ ከወሰዳቸው፤ ለጥናትና ምርምር ሥራው ማሳያ ይሆኑት ዘንድ አብዝቶ ከጠቀሳቸው፤ ለትንታኔው ይበጁት ዘንድም በስፋት ካብራራቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል የሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ሥራዎች በርካቶች ናቸው። በተለይ ከሰይፉ ሥራዎች ጎልቶ ከሚታወቅለት "ውስጠት" መድበሉ ውስጥ "ልዩ-'ቃ"ን ወስዶ በምንና በእንዴት አይነት ሁኔታ ለንባብ እንዳበቃው፤ ከቅርፃዊ መዋቅር አኳያ ሰይፉ ምን ያህል ከሌሎች የተለየ ገጣሚ እንደሆነ ለተመለከተ እውነትም ሰይፉ ለዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ፤ በዘርፉም ልዩ የሆነ ሥነጽሑፋዊ ማንነት (በተለይም ከወጥነት (ኦሪጂናሊቲ) አኳያ) እንዳለው ወዘተ አፍታም ሳይቆይ ይገነዘባል።

በክፍል 2 "ሥነግጥምን ማንበብና ማድነቅን መማር" ከሚለው የምዕራፉ ዐቢይ ርዕስ ስር በማጠናከሪያነት የሰይፉን "በማንኛውም ባህል ማለት ይቻላል–የደህና ግጥም ንባብ፣ ሙዝ ላጥ-ዋጥ ሊሆን አይችልም-የሆነ ፅነት ወይም አስቸጋሪነት ይኖረዋል።" የሚለውን ለሚጠቅሰው ለብርሃኑ ገበየሁ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ለብዙዎቻችን ያልተለመደና እንግዳ የሆነ የአገጣጠምና የቋንቋ አጠቃቀም ብልሀትን ይዞ የመጣ፣ አፈንጋጭ ... (ገፅ 44 እና ሌሎችም)፣ "ብርቱ ገጣሚ" (ገፅ 130) ሲሆን፤ በአማርኛ ሥርዓተ ጽሑፍ ውስጥ ያልተለመደ ደማቅ ነጥብ (ስንኞች በ'..' መታጠራቸውን) ይዞ የመጣ (ከላይ የጠቀስንለትን የገጣሚውን "አበርክቶት" ያስታውሷል)፤ ይህም በእስከ ዛሬው የአማርኛ ሥነግጥም ጉዞ በራሱ ያልተለመደና አስገራሚ ነገር (ገፅ 42) የሆነ ሲሆን ይህንን ያስተዋወቀው ደግሞ ሰይፉ እንጂ ሌላ አይደለምና ለዘርፉ ባለ ትልቅ ውለታ ነው።

የሰይፉን ሥራዎች ስንመለከት የየራሳቸው ቀለምና አሻራ ያላቸው ሆነው የምናገኛቸው ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቃላት ስደራው፣ ፈጠራውና አጠቃቀሙ ይገኙበታል።

ሰይፉ ቃልን ከቃል በማገናኘት አንድ እራሱን የቻለ ጽንሰ ሀሳብ መፍጠር የተካነበት ሲሆን፤ ይህም ከ"አፈር ያነሳ ሥጋ" እና ከ"ውስጠት" በተለየ መልኩ በ"የተኳጎጠ ልብ" ውስጥ ጎልቶ ይታያል። "ስንከን" (art) አንዱ ሲሆን "ሰንካኞች" (artists) ለሚለው ይውል ዘንድ አስቦበት ተግባራዊ ያደረገ ገጣሚ ነው። ("ሥንኪን" ከ"ሥን" እና "ኪን" ውህደት የመጣ ወይም የተፈጠረ ጽንሰ ሀሳብ ነው። "ሥነጥበብ" እና "ኪነጥበብ"ን ያስቧል፤ ከሁለቱም የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ እንደተወሰዱና ውህደት እንደፈጠሩም ልብ ይሏል።) ይህንን ከራሱ፣ ከሥነግጥም መድበልነቱ ባለፈ በሁሉን አቀፍነቱ (ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ፖለቲካ፣ ባህል ...) ከሚታወቀው፣ ከ"የተኳጎጠ ልብ" አንድ አንቀፅ ወስደን እንመልከተው፤

ዛሬ ለኢትዮጵያዊነት የቆመ ሁሉ፣ ብሔራዊ እርስበቱ (ideal) "አፈር ያነሳ ሥጋ" ሆኖበት እሚያደርገውን ያጣ ይመስላል። እንግዲህ፣ ይህ ሁኔታ ባስከተለባቸው ተኳጉጦት ነው ኃይሌና ዮፍታሔ እና እነሱን የመሰሉ ሰንካኞች (artists) ያኔ በኢጣሊያን ወረራ፣ ታዬና ሰይፉ እና እነሱን የመሰሉ ደሞ፣ ዛሬ በወያኔ/ኢሕአዴግ ተመሳሳይ ሥንከን-ዕዝል ስሜት ገልጸው የነበሩና የሚገልጹ። ይህም፣ የሁለቱ ዘመናት በሃገር መፍረስ መመሳሰል የቀሰቀሰው የሠንካኞች የሥዕል ቡርሽና የቅኔ ብዕር መሆኑ ነው። ቅብብሎሹ አምሮ ዳብሮ መቀጠል አለበት። (ገፅ 26 - የጀርባ ሽፋኑ ላይም ወጥቷል።)

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ይታወቃል ከተባለ እንኳን የሚታወቀው በገጣሚነቱ እንጂ በፎክሎር ምሑርነቱና ተመራማሪነቱ አይደለም። ይህን ስንል ሰይፉ በዚህ ዘርፍ በርካታ ሥራዎችን የሠራና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ በመሆኑ ሲሆን፤ ለዚህም ለዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀው (እኔ ያገኘሁት "የፎክሎር (1) መዝገበ - ቃላት ጥንቀራ ቅድመ ዝግጅት" በሚል ርዕስ የቀረበውንና በ"የፎክሎር ሙያነክ ቃላት" ላይ የሚያተኩረውን ሰፊና ጥልቅ ጥናት ነው።)

ሰይፉ በሃያሲነቱም በራሱ መንገድ እንጂ በተቀደደለት የመሄድ ፍላጎት እንደሌለው በበርካታ ሥራዎቹ ውስጥ ይታያል። ለምሳሌ ቀደም ሲል የእነ ገብረክርስቶስን ሥራዎች ባሄሰበት ጽሑፉ (አንድምታ ልሳን፣ ቁጥር 7) ውስጥ እንደምንመለከተው የሰነዘረው ሂስ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ሲሆን አንዱም አሰነኛኘትን የተመለከተው ነው። ሰይፉ ይህንን ክፍል በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍሎ ሥራዎቹን የመረመረ ሲሆን፤ ከእነሱም "ሰያፍ ስንኝ"፣ "ስንኝ-አጠፍ ስንኝ"፣ "ቁልቁሎሽ ስንኝ" እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

ነገሩ፣ ዶክተር ዮናስ አድማሱ "ከሚቀር ይጥቆር" እንደሚለው ነው። ይህች ሚጢጢዬ የጋዜጣ ገጽ ላይ ጽሑፍ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬውን ትገልፃለች ብሎ ማንም ለክርክር አደባባይ አይወጣም። የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ አላማ ባለውለታዎቻችንን ማስታወስና ለአዲሱ ትውልድ ማቀበል፤ ከተሳካልንም የጥናትና ምርምር ሰዎች፣ ደራሲያን ... ገፋ አድርገው እንዲሄዱበት ማድረግ ... እንጂ የባለ ውለታዎቻችንን ሙሉ በኩለሄ እንሸፍናለን ማለት አይደለም። የዛሬው ባለውለታችንም ጉዳይ እንደዛው ነው። ወደ "አንቱ"ታችን በመመለስ እናጠቃለው።

እጅግ የረቀቁ፣ ውለታቸው ከፍ ያለ፣ በዘርፉ ሁሉን አወቅ፤ ነገር ግን የሥራቸውን ያህል ምንም ያልተነገረላቸው፤ በአካባቢውና በጥናት መስኩ አካባቢ ባሉ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ብዙም ያልተወሳላቸው፤ በዚህ የሰው ዘፈን ወስዶ አደባባይ በሚወጣበት ዘመን ስለ እሳቸው ምንም ያልተፃፈላቸው ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ባለትዳር እና የአራት ልጆች አባት እንዲሁም የአራት ልጆች አያት የነበሩ ሲሆን፤ የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው በስደት በኖሩበት በዩናይትድ ስቴትስ አትላንታ ጆርጅያ ተፈፅሟል።

# ስፖርት


## የአካባቢን እግር ኳስ ያነቁት የፈረንሳይ ለጋሲዮን እና የኮልፌ ውድድሮች

**አቤል ገብረኪዳን**

ባለፈው እሁድ በአዲስ አበባ ሁለት አንጋፋ ሰፈሮች የተዘጋጁ የወጣቶች የእግር ኳስ ውድድሮች የፍጻሜ ፍልሚያዎች ተካሂደዋል። በሁለቱም ቦታዎች በብዙ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ ተገኝቶ የታደመ ሲሆን ብዙ ዝነኛ ሰዎች፤ የመንግሥት ኃላፊዎች፤ አርቲስቶች እና ሌሎችም በክብር እንግድነት ተሳትፈዋል።

በመጀመሪያ ወደ ፈረንሳይ ለጋሲዮኑ ውድድር እንጓዝ። ውድድሩ ዘንድሮ ሲካሄድ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። አዘጋጆቹ እንደሚሉት ከሆነ ለመጨረሻ ጊዜ ተመሳሳይ ውድድር በአካባቢው የተካሄደው ከ24 ዓመት በፊት ሲሆን ከዚያ በኋላ ካቻምና የተካሄደው ውድድር የመጀመሪያው የዘንድሮው ደግሞ ሁለተኛው ነው። ውድድሩ የተካሄደበት የጨፌ ዞናል ስቴድየም ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የፈረንሳይ አካባቢ ወጣቶች የተጫወቱበት እና ባለፈው አመት በአዲስ መልክ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተገንብቶ ሥራ ላይ የዋለ ነው። እሁድ እለት በተካሄደው የፍጻሜ ጨዋታ ላይ ሜዳው በሕዝብ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ሲታይ የአካባቢው ነዋሪ ይህን ጊዜ ምን ያህል ናፍቆት እንደነበር ምልክት ነው።

የውድድሩ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆነውን ወጣት ሀብታሙ ጌታቸውን ‹‹የዚህ ውድድር አላማ የፈረንሳይ ለጋሲዮን ወጣት መልሶ ወደ ስፖርት እንዲመጣ ማድረግ ነው። በአሁኑ ወቅት ወጣቱ በመዋያ እጦት ወደ ሱስ እና ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች ውስጥ እየገባ ነው። ስለዚህም ይህን ለመመከት በታዳጊዎች ላይ የተመሠረተ ውድድር ማዘጋጀት አለብን። በዚህ ውድደር 12 ቡድኖች፤



**በፈረንሳይ ለጋሲዮን በጨፌ ዞናል ስቴድየም የተካሄደውን ውድድር በርካቶች በስፍራው ተገኝተው ተከታትለውታል፣**

በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች እና በብዙ ሺ የሚቆጠር ታዳሚ ተሳትፎበታል። በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ያሉ የፈረንሳይ ለጋሲዮን ልጆች ወጣቶቹን በብዙ ደግፈዋል። በዚህም የተነሳ ውድድሩ ደማቅ ሆኖልናል። ትልቅ መነቃቃትም ፈጥሯል›› በማለት ለአዲስ ዘመን አስተያየቱን ሰጥቷል።

በቀጣይ አካባቢውን የሚወክል እና በሊግ የሚወዳደር የእግር ኳስ ክለብ ለመመስረት ጥረት ላይ እንደሆኑ የሚናገረው ወጣት ሀብታሙ የሜዳውን አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕዝባዊ ለማድረግም ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን ገልጿል። በእለቱ በውድድሩ ላይ ታዳሚ የነበረችው አርቲስት ፋንትሽ በቀለ እና እህቶቿ ለፍጻሜ ለደረሱት ቡድኖች የትጥቅ መግዣ የ100ሺ ብር ስጦታ አበርክተዋል።

በኮልፌ የተካሄደው ውድድር ደግሞ ኢምር በኮልፌ ቶርናመንት የተሰኘ ሲሆን የፍጻሜ ጨዋታውም በተለምዶ መላጣ ሜዳ በሚባለው አካባቢ ተካሂዷል። የፍጻሜውን ጨዋታም በሺ የሚቆጠር የኮልፌ እና አካባቢው ነዋሪ ታድሞበታል። ኮልፌዎች የውድድሩን ፍጻሜ ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ያላቸውን ክብር ለመግለጽ እንዲሁም ጀግኖቻቸውን ለማክበር ተጠቅመውበታል። ምስጋናው ከተቸራቸው መካከል አንጋፋው ደራሲ ሀይለመለኮት መዋእል፤ ‹‹የወታደር ልጅ ነኝ›› በሚል የግጥም መድብል የምናውቃት ሻለቃ ወይንሀረግ፣ የቀድሞ ቦክስ አሰልጣኝ ኢንስፔክተር ሰለሞን፣ የአሜድላ ስፖርት ክለብ መስራች አቶ አስረስ ተጠቃሽ ናቸው። ውድድሩ በቆየበት ጊዜ ሁሉ የአካባቢውን ሕዝብ ትኩረት ይዞ የከረመ ሲሆን ብዙ ተስጥኦ ያላቸው ወጣቶች እና ታዳጊዎች መታየታቸው ተነግሯል።

አዲስ አበባ ከተማ በኢትዮጵያ የስፖርት ታሪክ በተለይም በእግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የሆኑ ስፖርተኞችን በማፍራት የምትታወቅ ሲሆን ነገር ግን ባለፉት ሁለት አስርት አመታት እነዚህን ስፖርተኞች ያፈሩ ሜዳዎች በተለያየ ምክንያት ለሌላ አገልግሎት ውለው ወጣቱ በመዋያ እጦት ሲንገላታ እንደኖረ ይታወቃል። ተተኪ ስፖርተኞች የማፍራት እድሉም እየተመናመነ ሲሄድ እንደቆየ የሚታወቅ ሀቅ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የሜዳዎቹ መጥፋት እንደዚህ ዓይነት ውድድሮችም አብረው እንዲጠፉ በማድረግ ወጣቱ በጋራ የሚገናኝበትን እድል እንዲያጣም አድርገውታል። በቅርብ ጊዜያት ግን ሁኔታዎች የመለወጥ እና አካባቢያዊ ውድድሮች የመመለስ አዝማሚያ እየታየባቸው ሲሆን ለዚህም ከላይ የጠቀስናቸው የፈረንሳይ ለጋሲዮን እና የኮልፌ ውድድሮች ማሳያ ናቸው።

መንግሥት በቅርቡ ከጀመረው የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት ውድድሮች ባሻገር እንዲህ ዓይነት ውድድሮችን መደገፍ እና ጤናማ ትውልድ እንዲፈጠር ማገዝ እንዳለበት ይታመናል። ባለሀብቶች በጥቂት ክለቦች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከመገፍገፍ እንዲህ ዓይነት ውድድሮችን በመደገፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም የስፖርት ቤተሰቡ እምነት ነው። አሰልጣኞች እና ክለቦችም ውሏቸውን እንዲህ ባሉ ቦታዎች በማድረግ አዳዲስ ተስፈኛ ወጣቶችን ከየሰፈሩ መመልመል እንደሚገባቸው አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። ይህን ማድረግ ከተቻለ አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ እግር ኳስም ሆነ ለመላው ስፖርት የሚጠቅሙ ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራት እንደምትችል እርግጥ ነው።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በከሠረው ሆላንድ ካር ኃ. የተ. የግል ማህበር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ንግድ ችሎት በመ/ቁጥር 20082o በሆነ በዋለው ችሎት የመክሠር ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ማህበሩ ያለበትን ዕዳ መክፈል እንዲቻል ከታች በሠንጠረዥ ውስጥ የተገለጹትን በ2 ኮንቴይነሮች ውስጥ ሞጆ ደረቅ ወደብ በጉምሩክ ኮሚሽን ታሽገው የሚገኙ ያልተገጣጠሙ አዲስ 6 መኪናዎች ባሉበት ሁኔታ በግልጽ ሐራጅ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ. | VIN የሻንሲ ቁጥር | ሞዴል | የሞተር ቁጥር | የመጫን አቅም | የነዳጅ አጠቃቀም በሊትር | የተመረተበት ጊዜ እ.ኤ.አ | የሐራጅ መነሻ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | L J16AA4C7102132 | HFC6512A4ACBF | HFC4GA3-1C | 7 | 2.0 | 2012 | 1,576,904.33 |
| 2 | LJ12EK17C4303593 | HFC7130LIF | HFC4GBI-3C | 5 | 1.3 | 2012 | 606,702.91 |
| 3 | LJ12GAS43C4004751 | HFC7200CIT | 4G6354N | 5 | 2.0 | 2012 | 1,576,904.33 |
| 4 | LJ12GA543C4004790 | HFC7200SF | HFC4GA3-IC | 5 | 2.0 | 2012 | 1,576,904.33 |
| 5 | LJ12FKT32C4C4100750 | HFC7200CIT | 4G654N | 5 | 2.0 | 2012 | 1,576,904.33 |
| 6 | LJ16AA3C2C7025959 | HFC6500KR3T | HFC4AA1-2BI | 12 | 2.8 | 2012 | 2,121,985.21 |

ማሳሰቢያ

1. ተጫራቾች በ2 ኮንቴይነር ውስጥ ያሉትን ለሽያጭ የቀረቡትን ያልተገጣጠሙ መኪናዎች በአንድ ላይ ለመግዛት ይጠበቅባቸዋል
2. ለሐራጅ የተመዘገቡ ተጫራቾች በራሳቸው ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው አማካይነት ሐራጁን መሳተፍ ይችላሉ፡
3. ለሐራጅ የቀረቡት ከላይ በሰንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሱት ያልተገጣጠሙ አዲስ መኪናዎች በኮንቴይነር ቁጥር PCIU8104418 እና በኮንቴይነር ቁጥር PCIU8405453 ውስጥ በጉምሩክ ኮሚሽን አማካይነት ታሽገው ሞጆ ደረቅ ወደብ ጉምሩክ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን የሐራጅ መነሻ ዋጋ 1/8 (አንድ ስምንተኛ) የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተመሰከረለት የክፍያ ማዘዣ (ሲ.ፒ.ኦ.) በከሠረው ሆላንድ ካር ኃ. የተ. የግል ማህበር ስም በማሠራት ከግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም. ባሉት ቀናት ከጠዋቱ 3፡oo እስከ 10፡00 ሰዓት ድረስ ልደታ ፍሊንትስቶን ሕንፃ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 514 በሚገኘው ቢሮ መመዝገብ አለባቸው፡፡
5. የንብረቶቹ የሐራጅ ሽያጭ ሰኔ 18 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡oo ጀምሮ የሚካሄድ ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች በዕለቱ ይሸጣል፡፡
6. የሐራጅ አሸናፊዎች የሚፈለገውን ክፍያ ከፈፀሙ በኋላ ንብረቶቹን በ10 ቀናት ውስጥ ከቦታው ላይ ማንሳት አለባቸው፡፡
7. ማንኛውም የስም ማዛወሪያ፣ ያልተከፈለ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ቫት እና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች የሐራጅ አሸናፊ መክፈል ይጠበቅበታል፡፡
8. የተሽከርካሪና ማሽነሪዎች የባለቤትነት ስም እንዲዛወር ንብረት ጠባቂው ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ደብዳቤ ይጽፋል
9. ማህበሩ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ሐራጁን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0911 125677፣ 0928 821709፣ 0911 664807 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፣**

## የከሠረው ሆላንድ ካር ኃ. የተ. የግል ማህበር ጽ/ቤት